

# ተሸናፊው ማነው?
# እኛ? ወይስ
# ሰላማዊ–ትግል?

ልደቱ አያሌው

መጋቢት 11 2016 ዓ.ም

# ተሸናፊው ማነው?
# እኛ? ወይስ
# ሰላማዊ-ትግል?

## ምጥን ሐሳብ

አገራችን ለምትገኝበት ሁለንተናዊ ኋላ-ቀርነት አንዱና ዋናው ምክንያት ከእርስ-በርስ ጦርነት አዙሪት መውጣት አለመቻላችን ነው። ከዓለም የፖለቲካ የታሪክ ሂደትና በመስኩ ከተካሄዱ በርካታ ጥናቶች እንደምንረዳው ጦርነት ቢበዛ አንድን በስልጣን ላይ ያለ አገዛዝ ከስልጣን ከማስወገድ ባለፈ ዘላቂ ለውጥናመፍትሄ ለማምጣት አያስችልም።

ጦርነት የሚያስከትለው ሰብዓዊና ቁሳዊ ቀውስ እጅግ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በትውልዱ ላይ አስከትሎት የሚያልፈው ስነ-ልቦናዊ ቁስልና ስብራት በቀላሉ የሚድን አይደለም።

በአንፃሩ፣ ሰላማዊ ትግል በበቂ ዝግጅትና በአግባቡ ከተካሄደ በአጭር ጊዜና በቀላል መስዋእትነት ለዘላቂ ለውጥ የማብቃት ዕድሉ ሰፊ እንደሆነ የሚያሳዩ በርካታ ተሞክሮዎች አሉ። በዚህም ምክንያት ሰላማዊ ትግል ከሞራልም ሆነ ከስልት አዋጭነት አኳያ ከጦርነት ይልቅ ተመራጭ መሆኑ በአብዛኛው የዓለም ህዝብ ዘንድ ሰፊ ተቀባይነት አግኝቷል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ግን ከአብዛኛው ዓለም በተቃራኒ በመቆም ሰላማዊ የትግል ስልትን የፈሪዎችና የአላዋቂዎች ምርጫ አድርገን በመቁጠር ከፖለቲካ ጨዋታ ውጭ አድርገነዋል። ዛሬም እንደ ትናንቱ ጦርነትን ብቸኛ የመፍትሄ መሳሪያ አድርገን በመቁጠር እርስ-በእርስ የመገዳደሉን አዙሪት የበለጠ አጠናክረን ቀጥለንበታል። በአሁኑ ወቅት "ነፃ እናወጣሃለን"ወይም "እናበለጽግሃለን"የምንለው ህዝብ በጦርነትና ጦርነትን ተከትለው በሚመጡ አደጋዎች በግፍ እያለቀ ይገኛል። እንታገልልሃለን የምንለው ህዝብ በጦርነት፣ በረሃብና በበሽታ ካለቀ በኋላ ማንን ነፃ ልናወጣና ልናበለጽግ እንደምንችል ግራ አጋቢ ሆኗል። ይህ አሳዛኝ ሂደትም ኢትዮጵያውያን ከዚህ ዓይነቱ የጦርነት አዙሪት ለመውጣት ያልቻልንበት ምክንያት "የሃሣብ መቀንጨር ነው ወይስ የስነ-ልቦና መቃወስ?" የሚል ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል ነው።

በአጠቃላይ አሁን ላይ የገባንበት በአያሌ መገናኛ ብዙሃን የታጀበ ብሄር-ተኮር ጦርነት እንደ ቀድሞዎቹ ጦርነቶች ነባር ችግሮቻችንን በማስቀጠል ወይም ወደ ሌላ አገዛዝ በማሸጋገር ብቻ የሚቋጭ ሳይሆን አጠቃላይ ህልውናችንን ሊያሳጣን እንደሚችል ግልፅ እየሆነ መጥቷል። ህዝብ ከአሰቃቂ እና ከባሰ እልቂት፣ አገርም ከመፈራረስ መዳን ካለባቸው የወቅቱን የእርስ-በእርስ ጦርነት በሃቀኛ ድርድር በአስቸኳይ ማቆም አለብን። ከዚያም ከስነ-ልቦናዊ ቁስልና ስብራት አድኖ ለዘላቂ መፍትሄ ወደሚያበቃን ሁሉን አቀፍ የሆነ አዲስ የሽግግር ሂደት ውስጥ መግባት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ሌላ ምትክ የሌለው ግዴታችን ነው።

# መግቢያ

**"ስለማላምንበት የኃይል ተኮር የትግል ስልት ላስተምራችሁ አልችልም። እኔ የማስተምራችሁ የህይወት ዋጋ የሚያስከፍላችሁ ቢሆንም እንኳ ለማንም ኃይል አንገታችሁን እንዳትደፉ ብቻ ነው" -[ማሃትማ ጋንዲ]**

ከደርግ ዘመን ጀምሮ ካናዳ የሚኖር ታላቅ ወንድም አለኝ። ከረዥም ቆይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ የተመለሰው በ1992 ዓ.ም ላይ ነበር። አዲስ አበባ ገብቶ ለአንድ ሳምንት ያህል ከእኔ ጋር በመኪና ሲዘዋወር ከሰነበተ በኋላ "ውይይት" ታክሲ መጠቀምና ከህዝቡ ጋር ተቀላቅሎ መዋል ፈለገ። እኔም ብዙ እንደማይመቸው ባውቅም "ሞክረው" አልኩት።

ለሶስት ቀናት ያህል የታክሲ አገልግሎት ሲጠቀም ከሰነበተ በኋላ "ህዝባችን ምን ነካው?" በማለት በመገረም ጠየቀኝ።

"ምነው?" አልኩት በምላሹ።

"ታክሲ ውስጥ ገብቼ ተሳፋሪዎቹን እንዴት አደራችሁ ስላቸው መልስ አይሰጡኝም። እንዲያውም በመገረምና በቁጣ ያዩኛል። ፈገግታ የሚያሳይም የለም። አንዱ ከሌላው ጋር ሲነጋገርም በኃይለ ቃል ነው። ከመቼ ወዲህ ነው ህዝቡ እንዲህ የተለወጠው?" አለኝ በሀዘን ስሜት።

የተዘጋጀሁበት መልስ አልነበረኝምና "ህዝቡ ተለውጦ አይመስለኝም፤ አንተ ተለውጠህ ስለመጣህ እንዳይሆን" አልሁት በደፈናው።

"ስማኝ!" አለኝ በሙሉ ልብ እንዳዳምጠው በመፈለግ ስሜት እየተመለከተኝ። እኔም ቀና ብዬ አይን አይኑን እያየሁ አዳመጥኩት።

"ፖለቲካ ውስጥ ገብተህ የምትደክመው በከንቱ ነው፤ ጊዜህን ባታጠፋ ይሻልሃል" አለኝ ቁጭት በተሞላበት ስሜት።

"ለምን እንዲህ አልክ?" አልኩት በመገረም።

ትንፋሹን ለጥቂት ሰከንዶች ሰብሰብ ለማድረግ ሞከረና - "ይኸ ህዝብ አሁን የሚያስፈልገው ፖለቲካ አይደለም። አብዛኛው ህዝብ ታሟል። የሚያስፈልገው ፖለቲካ ሳይሆን የስነ-ልቦና ህክምና ነው" አለኝ በእርግጠኛነት ስሜት።

ይህንን የወንድሜን አባባል በጊዜው የተለመደ የዲያስፖራ መመፃደቅ አድርጌ ስለቆጠርኩት ብዙም ትኩረት ሳልሰጠው ፈገግ-ብዬ እንደዋዛ አለፍኩት።

ይህ ከሆነ 24 ዓመት ሆነው። እንደ ግመል ሽንት ወደ ኋላ የሚሄደውን የአገራችንን ፖለቲካ ሳስብ የታላቅ ወንድሜ የያኔው አባባል አንዳንድ ጊዜ ጆሮዬ ላይ ያቃጭልብኛል።

የወንድሜ አባባል ምክኒያታዊ ነበርን? ብዬ ራሴን እጠይቃለሁ። እስኪ ባለሞያዎቹም ሆናችሁ አንባብያን ተነጋገሩበት።

ብዙውን ጊዜ ራሴን እንደተሸነፈና እንደወደቀ ፖለቲከኛ አድርጌ እንደምቆጥር በአደባባይ ስናገር ብዙዎች ንግግሬ ልባዊ ሳይሆን ስላቅ ይመስላቸዋል። እኔ ግን ከልቤ ነው። ምክንያቱም ለ31 ዓመት ያህል ሁለንተናዬን ሰጥቼ በፖለቲካ ትግል ውስጥ የቆየሁት በዋናነት የእርስ-በርስ ጦርነትና የብሔርተኝነት ፖለቲካ ከአገራችን ተወግዶ በምትኩ የሃሳብና የመቻቻል ፖለቲካ እንዲሰፍን የበኩሌን

ድርሻ ለመወጣት ነበር። ነገር ግን ሙሉ የወጣትነት ዕድሜዬን ለጠየቀ ረዥም ጊዜ በሙሉ ትኩረትና ትጋት ታግዬ ለአገሪቱ ትርጉም ያለው ለውጥ አላመጣሁም። አገሪቱ ዛሬ ላይ እኔ ወደ ፖለቲካ ትግል ከገባሁበት ወቅት በብዙ ርቀት በብሄርተኝነት ስሜት ተከፋፍላ የከፋ የእርስ-በርስ ጦርነት ውስጥ ገብታለች። በዚህም ምክንያት በዘንድሮው የዓለም አቀፍ የሰላማዊነት መመዘኛ (Global Peace Index, 2023) ኢትዮጵያ በሰላም ጉዳይ ምዘና ከተደረገባቸው 163 የዓለም አገራት ውስጥ በሰላም እጦት 151ኛ ደረጃ ላይ ተቀምጣለች።

ኢትዮጵያ እንኳንስ ሰላማዊ ወደሆነ ሁኔታ ልትሸጋገር ይቅርና 'እንደ አገር ህልውናዋ ይቀጥላል፣ አይቀጥልም?' የሚል ጥያቄና ፈተና ላይ ወድቃለች። እኔም እንደ አንድ ፖለቲከኛ ለ31 ዓመት ሰላማዊ ትግልን ስሰብክና ሳካሂድ ከኖርኩ በኋላ ዛሬ ላይ እንደገና ወደ ኋላ ተመልሼ ስለ ሰላማዊ ትግል አስፈላጊነትና አዋጭነት ለመከራከር ተገድጃለሁ። ለአንድ ሙሉ የወጣትነት ዕድሜውን በትግል ውጣ-ውረድ ላሳለፈ ሰው ከዚህ በላይ ሽንፈትና ኪሳራ ያለ አይመስለኝም። እንዲያውም "የህይወት ዘመን ኪሳራ" ሊባል የሚችል ነው።

በእኔ በኩል "ይህንን ሳላደርግ ቀረሁ" ብዬ በግሌ የምፀፀትበት ነገር ባይኖርም የተመኘሁትና የታገልኩለት ዓላማ የትም ሳይደረስ በመቅረቱ ግን ከፀፀትም በላይ ጥልቅ ሀዘንና የተሸናፊነት ስሜት ይሰማኛል። ለአሸናፊነት የበቁት ጦረኞችና ብሄርተኞች ስለገደሉት "ጠላት" በኩራት ሲፎክሩ፣ ስለተቆጣጠሩት ተራራና ከተማ በደስታ ተሞልተው ሲናገሩ ስሰማ በእርግጥም ሽንፈቴ አጥንቴ ድረስ ዘልቆ ይሰማኛል። ለዚህም ነው ስለተሸናፊነቴ ህዝብን በአደባባይ ይቅርታ የጠየቅሁት። ይህንን በማድረጌም በደካማነት እንጂ ራሴን በጥፋተኛነት አልወቅስም። ሁኔታዎች እንዲለወጡ አቅምና ሁኔታ በፈቀደልኝ መጠን በመታገሌና እስካሁንም የብሄርተኝነት ፖለቲካና የየትኛውም የእርስ-በርስ ጦርነት ደጋፊ በመሆን የጥፋት ተጋሪ ባለመሆኔም እርካታና ኩራት ይሰማኛል። ይህ ሁሉ ግን ተሸናፊና ወዳቂ ፖለቲከኛ የመሆኔን እውነታ አይቀይረውም።

የእኔ ዕይታ ይህ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ሽንፈቱን የእኔና የእኔን መሰል ሰዎች ብቻ አድርጋችሁ የምታዩ ወገኖች ካላችሁ ግን እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት ግብዝነት ይሆናል። ውድቀቱና ሽንፈቱ እንደ አገርና ህዝብ የጋራ ነው። ጦረኞችና የጦርነት ተባባሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ታግለን አሸናፊ መሆን ባለመቻልም ሆነ ዝምታን በመምረጥ አገሪቱ አሁን ላይ ወደምትገኝበት ምስቅልቅል እንድትገባ የፈቀድን ሁሉ ተሸናፊዎችና ተጠያቂዎች ነን።

በአሁኑ ዘመን አብዛኛው ዓለም የሰላማዊ የትግል ስልትን ተገቢነትና አዋጭነት ከመገንዘብም አልፎ የችግሮቹ ብቸኛ የመፍትሄ መሳሪያ አድርጎ እየተጠቀመበት ይገኛል። ለዚህም ነው የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በቁጥር A/Res/61/271 ውሳኔ መሰረት October 2ን (ጥቅምት 2ን) Non-Violence Day (ዓለም አቀፍ የሰላማዊ ትግል ቀን) አድርጎ የሰየመው። እኛ ግን ከአብዛኛው ዓለም በተቃራኒ ሰላማዊ የትግል ስልትን እንደ ፈሪዎችና አላዋቂዎች ምርጫ አድርገን በመቁጠር የጠላነውና የተጠየፍነው ከመሆኑም በላይ ኃይልንና ጠብመንጃን ዛሬም ዋና የመፍትሄ መሳሪያ አድርገን በመቁጠር እርስ-በርስ መገዳደሉን ቀጥለንበታል። ይህም ከራሳችንም ሆነ ከሌሎች ተደጋጋሚ ጥፋትና ውድቀት መማር የተሳነን መሆኑን ከማሳየት በላይ "ችግራችን የፖለቲካ ግንዛቤ መቀንጨር ነው ወይንስ የስነ ልቦና መቃወስ?" የሚል ጥያቄ እንዲነሳ የሚያስገድድ ነው።

አገራችን ኢትዮጵያ በዓለማችን ካሉ ጥቂት ገናና፣ ጥንታዊና የስልጣኔ መነሻ ከሆኑ አገሮች ውስጥ አንዷ ነች። አብዛኞዎቹ ጥንታዊም ሆኑ አዳዲስ አገራት ከፍተኛ የስልጣኔ ደረጃ ላይ በደረሱበት በአሁኑ ዘመን እኛ ግን በየትኛውም ዓይነት የዘመናዊነትና የእድገት ደረጃ መመዘኛ የዓለም ጭራ ሆነን ቀጥለናል። የዛሬ 10 ሺህ ዓመት ገደማ የጀመርነውን በሬ ጠምዶ በሞፈር ቀንበር የማረስ ስልተ-ምርት እስካሁን ድረስ መቀየር ተስኖን በምግብ እንኳን ራሳችንን መቻል የተሳነን ተመፅዋቾች ሆነን

ለመኖር ተገደናል። በልተን ማደር አለመቻላችን አልበቃ ብሎ ሌሎች በስልጣኔ ተራቅቀው የሰሩትን ድሮንና ታንክ ከድሃ ህዝብ ጉሮሮ በተቀማ ገንዘብ እየሸመትን እርስ-በርስ መገዳደሉን አጠናክረን ቀጥለንበታል።

ለዚህ ሁሉ ውድቀት የዳረገን አንዱና ዋናው ምክንያት ያልተቋረጠ የእርስ-በርስ ጦርነት ቢሆንም እኛ ግን ግብዞች ነንና የችግራችን ዋና ምንጭ በሆነው ጦርነት ችግራችንን እንፈታለን ብለን በማሰብ ዛሬም በሌላ የጦርነት አዙሪት ውስጥ ገብተን እየዳከርን እንገኛለን። ሌላው ዓለም ከሰው አልፎ ከስነ-ምህዳር ጋር እንዴት ተስማምቶ መኖር እንዳለበት፣ ሰው ሰራሽ አሳቢነት (AI – Artificial Intelligence) በሰው ልጅ የወደፊት ህልውና ላይ የሚኖረው ጥቅምና ጉዳት ምን ሊሆን እንደሚችል ተጨንቆ እያሰበ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት እኛ ግን "የጦርነት ጥሩ፣ የሰላም መጥፎ የለውም" (There never was a good war, or a bad peace - Benjamin Franklin) የሚለውን የፖለቲካ "ሀ…ሁ…" መገንዘብ ተስኖን "ጦርነት ይሻለናል ወይንስ ሰላማዊ ትግል?" የሚል ዘመኑን ያልዋጀ ደካማ ውዝግብና ክርክር ውስጥ እንገኛለን።

ለአንድ ለ31 ዓመት ያህል በሰላማዊ ትግል ሂደት ውስጥ ላለፈ የፖለቲካ ሰው እንዲህ ዓይነቱ ክርክር ውስጥ ገብቶ መገኘት "ከውሃና ከአረቄ የትኛው ለጤና ይጠቅማል?" ብሎ የመከራከር ያህል የማይመጥንና የስሜት ምቾች የማይሰጥ ቢሆንም የዛሬው መጣጥፌ ትኩረት ግን በዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ዙሪያ እንዲያጠነጥን ግድ ሆኗል።

በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ዐውድ ጦረኝነትን መደገፍ እንደ አገር ወዳድና ጀግና፣ በአንፃሩ ጦርነትን መቃወም እንደ አላዋቂና ፈሪ እንደሚያስቆጥር በሚገባ እገነዘባለሁ። ይሁንና ጄሲ ጃክሰን እንዳለው **"የሰላማዊ ትግል ስልት ዋና ትኩረት ጀግናና አገር ወዳድ መስሎ መታየት ሳይሆን ውድ የሆነውን የሰው ልጅ ህይወት ከጥፋት መታደግ"** መሆኑን ስለምንገነዘብ ዛሬም እንደትናንቱ የሰላማዊ ትግል ስልት ጠበቃ ሆኖ መቀጠልን መርጫለሁ። በአሁኑ ወቅት እንዲህ አይነቱን የሰላም አቋም ማራመድ "በጋለው ብረት ላይ ቀዝቃዛ ውሃ ጨመርክበት" የሚል ትችት ሊያስከትል እንደሚችል እረዳለሁ። በእርግጥም ፍላጐቴ እሱ ነው። የጋሉት ብረቶች መቀዝቀዝ አለባቸው። ይሁንና በእኛ አገር የወቅቱ ፖለቲካ ራስን ለውግዘትና ለሃሜት ሳያጋልጡ ህዝብን የሚጠቅም አጀንዳ ማራመድ አስቸጋሪ ነው። ግን ምን ይደረግ? እንዲህ ዓይቱን ዕዳ ለመሸከም ለአንዳንዶቻችን ግድ ሆኗል።

በማህበራዊ ሳይንስ "ሊለወጥ አይችልም" ሊባል የሚችል አመለካከት የለም። በዚህም ምክንያት የፖለቲካ ትግሉን ከተቀላቀልሁበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ የቀደሙ አመለካከቶችን አሻሽያለሁ ወይንም ቀይሬአለሁ። ለመለወጥ ሁልጊዜም አእምሮዬ ዝግጁ ቢሆንም ሰላማዊ ትግልንና የብሄርተኝነት ፖለቲካን በሚመለከት ያለኝን አቋም ሊፈታተን የሚችል አሳማኝ ክርክር ግን እስካሁን ገጥሞኝ አያውቀም። ወደፊትም የሚገጥመኝ አይመስለኝም።

መጣጥፌ የራሱ የመግቢያና የመደምደሚያ ክፍል ያለው ቢሆንም፣ በዋናነት በሶስት አበይት ርዕሶች ተከፍሎ የሚቀርብ ይሆናል። የመጀመሪያው **"ሰላማዊ ትግል ምን ማለት ነው? በምንስ ይገለጻል?"**፣ ሁለተኛው **"ሰላማዊ ትግል ከኃይል-ተኮር ትግል ይልቅ ለምን ይመረጣል?"**፣ ሶስተኛው ደግሞ **"በሰላማዊ ትግል ዙሪያ የሚነሱት አከራካሪ ሃሳቦች ምንድን ናቸው?"** የሚሉ ናቸው።

በዚህ መጣጥፍ ስለ ኃይል-ተኮር የትግል ስልት የሚቀርበው ትችት መንግስትንና ሁሉንም በአገሪቱ ያሉ ታጣቂ ኃይሎች የሚመለከት መሆኑን፣ ጦርነትን የሚመለከተው ትችትም የውስጥ የእርስ-በርስ ጦርነቶችን ብቻ የሚመለከት መሆኑን፣ ከታጣቂዎቹ ውስጥም "ጦርነት ውስጥ የገባነው ተገደንና አማራጭ አጥተን ነው እንጂ ጦርነት መፍትሄ ያመጣል ብለን አምነን አይደለም" ብለው ከልባቸው የሚያምኑትን የማይመለከት መሆኑን፣ ስለ ሰላማዊ ትግል ስልት የሚቀርበው አስተያየትም ለሲቪክ መብቶች መከበር የሚካሄድን እንቅስቃሴ ሳይሆን በዋናነት ለስልጣን ጥያቄና ለስርዓት ለውጥ በፖለቲካ

ኃይሎች የሚካሄደውን ትግል የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። እነዚህን ነጥቦች በአግባቡ ሳይገናዘብ ትችት የሚያቀርብ ሰው ችግሩ ከራሱ እንጂ ከእኔ አለመሆኑን መገንዘብ አለበት።

በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ያለልማዴ የውጭ ሰዎችን ጥቅስና አባባል ሰፋ ባለ መጠን ተጠቅሜአለሁ። ይህንን ያደረግሁት ስለ ሰላማዊ ትግል አዋጭነት ለመሟገት አገር በቀል የሆነ ልምድና ሃሳብ አጥሮኝ አይደለም። ይልቁንም የአገር ልጅን ሃሳብ እምብዛም ለማዳመጥና ለማክበር የሚፈልግ ወገን ያለ አልመስልህ ቢለኝ ነው።

**መልካም ንባብ!**

# 1.ሰላማዊ ትግል ማለት ምን ማለት ነው? በምን ይገለፃል?

**"ሰላማዊ ትግል አካላዊ ጥቃትን ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ጥቃትን ጭምር ማስወገድ የሚያስችል መሳሪያ ነው።" - *[ማርቲን ሉተር ኪንግ]***

ወደ ፅንሰ-ሃሣቡ ትርጉም ከመግባታችን በፊት በቅድሚያ ለተሻለ ግንዛቤ ይረዳ ዘንድ በግጭት /Conflict/ እና በኃይል-ተኮር ግጭት /Violence/ መካከል ያለውን ልዩነት በአግባቡ መረዳት ያስፈልጋል። "ግጭት" ተፈጥሯዊ የሆነ፣ መቼም ቢሆን ልናስወግደው የማንችልና ሁልጊዜም አብሮ የሚኖር ክስተት ነው። ብዙውን ጊዜ ግጭት የሚነሳው በፍላጐቶች አለመሟላት፣ በእውቅና ፍላጎትና በስልጣን ጥያቄ ወይም በጥቅምና በአስተሳሰብ ቅራኔዎች ምክንያት ነው።

ሁሉም ዓይነት ግጭቶች የግድ ወደ አካላዊ ግጭት ሊያድጉ አይችሉም። የጥቅምና የአስተሳሰብ ልዩነቶችን በውይይትና በድርድር የመፍታት ብቃት ያላቸው ግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች ግጭቶችን ያለአካላዊ ግጭት የመፍታት ዕድል የሚኖራቸው ሲሆን፣ እንደ እኛ አቅምና ፍላጐትን ያጡት ግን ወደ ኃይል-ተኮር ግጭት ይገባሉ። ስለዚህ ግጭት /Conflict/ አሉታዊ ብቻ ሳይሆን አዎንታዊም ገፅታና ሰፋ ያለ ይዘት ያለው አጠቃላይ ፅንሰ ሃሳብ ሲሆን፣ ኃይል-ተኮር ግጭት /Violence/ ግን በግጭት /Conflict/ ማዕቀፍ ውስጥ የሚገኝና አሉታዊ ገፅታ ብቻ ያለው ጠባብ ፅንሰ ሃሳብ ነው።

ስለዚህ በዚህ መጣጥፍ ውስጥ ስለ ሰላማዊ ትግል የሚቀርበው ሃሳብ ግጭት /Conflict/ ከሚለው አጠቃላይ ፅንሰ-ሃሳብ ጋር በተያያዘ ሳይሆን፣ ኃይል-ተኮር ግጭት /Violence/ ከሚለው አሉታዊና ጠባብ ክስተት በተፃራሪ የሚቀርብ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። በዚህ ላይ መግባባት ከፈጠርን የሰላማዊ ትግል ስልት ትርጉምን በአጭሩ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር።

ሰላማዊ የትግል ስልት ማለት አንድን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወይም ፖለቲካዊ ጥያቄና ዓላማ ሰላማዊና ግጭት-አልባ በሆኑ ስልቶች ለማሳካት የሚደረግ ትግል ነው። ሰላማዊ ትግል በጥቅሉ በህዝባዊ እምቢተኛነት፣ በጐዳና ላይ ተቃውሞ፣ በሥራ ማቆም አድማ፣ ለአሉታዊ ተግባራት ትብብር በመንሳት፣ ባልተገቡ ድርጊቶች ላይ ጣልቃ በመግባት፣ በውይይትና በድርድር፣ በምርጫ ተሳትፎና በተለያዩ መሰል ስልቶች የሚካሄድ ትግል ነው። ሰላማዊ የትግል ስልት - በህዝብ አሳታፊነቱ፣ በቀጣይ ሂደትነቱ፣ በህግ አክባሪነቱ፣ በመርህ ተገዥነቱ፣ ለሰው ልጅ ደህንነትና ክብር ተገቢ ዋጋ በመስጠቱና በመሰል መርሆዎቹ የሚታወቅ ስልት ነው።

ሰላማዊ የትግል ስልት ከጥንታዊ የቻይና፣ የግሪክና የሮማውያን ዘመን ጀምሮ እስከ አሁኑ የመረጃ ሳይንስ ዘመን ድረስ ባለው የታሪክ ሂደት እያደገና እየሰፋ የመጣ ስልት ነው። ሰላማዊ የትግል ስልት ከሞራል ወይም ከስልት አዋጭነት /Strategy/ ወይም ከሁለቱም መስፈርቶች አኳያ በመነሳት የሚመረጥና የሚካሄድ ስልት ነው።

አንጋፋው የሰላማዊ ትግል አርበኛ ማሃትማ ጋንዲ እንዳለው፤ "ሰላማዊ የትግል ስልት በሰው ልጆች እጅ ውስጥ ያለና በማንኛውም ጊዜ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል ታላቅ የለውጥ መሳሪያ ነው"። ሌላው የዓለማችን የሰላማዊ ትግል አርበኛ ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዳለው፤ "ሰላማዊ የትግል ስልት አካላዊ ግጭትን ብቻ ሳይሆን የሰውን ልጆች ውስጣዊ መንፈሳዊ ግጭትንም የመፈወስ አቅም ያለው ጠንካራ ስልት" ተደርጐ ይታያል። በአጠቃላይ ሰላማዊ የትግል ስልት በአሁኑ ዓለማችን ከፍትሃዊነትም ሆነ ከስልት ውጤታማነት አኳያ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ የትግል ስልት ሆኗል።

# 2. ሰላማዊ ትግል ከኃይል-ተኮር ስልት ይልቅ ለምን ተመራጭ ይሆናል?

**"የጦርነት ጥሩ፣ የሰላም መጥፎ ኖሮ አያውቅም። ጦርነት በተፈጥሮው አውዳሚ ነው"** - [ቤንጃሚን ፍራንክሊን]

ከዚህ በላይ በቀረበው ክፍል ለመግለፅ እንደተሞከረው ሰላማዊ የትግል ስልት ከሞራልም ሆነ ከስልት አዋጭነት /Strategy/ አኳያ ወይም በሁለቱም ምክኒያቶች ሊመረጥ የሚችል ስልት ነው። በኔልሰን ማንዴላ ዕይታ ሰላማዊ ትግል በዋናነት የሚመረጠው "ከስልት አዋጭነት አኳያ" ሲሆን፣ በማሃትማ ጋንዲ በኩል ግን ሰላማዊ ትግል በዋናነት የሚመረጠው "ከሞራል አኳያ" ነው። በእኔ ዕይታ በአሁኑ ዘመን የሚካሄድ ሰላማዊ ትግል ሁለቱንም መመዘኛዎች ታሳቢ ያደረገ ሊሆን ይገባዋል። ከፖለቲካ ትግል አኳያ ዋናው መመዘኛ የስልቱ ውጤታማነት ቢሆንም ሞራላዊ ጉዳዮችም ጠቃሚ ስለሆኑ ተገቢ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

ሰላማዊ ትግል መድረሻ ውጤቱ ብቻ ሳይሆን መሄጃ መንገዱም ትልቅ ፋይዳ ያለው ስለሆነ ስልቱን ለመምረጥ የምንጠቀምበት መመዘኛ ለሞራልም ሆነ ለስልት ውጤታማነት ተገቢ ትኩረት ሊሰጥ ይገባዋል። ስለሆነም ከእነዚህ ሁለት መሰረታዊ መመዘኛዎች አኳያ ኃይል-ተኮር ከሆነ የትግል ስልት ይልቅ ሰላማዊ የትግል ስልትንመምረጥ ለምን ተገቢና ጠቃሚ እንደሚሆን እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር።

## 2.1. ሰላማዊ ትግል ከሞራል አኳያ

***"ሌሎች ፍጡራንን መጉዳት እስካላቆምን ድረስ እኛአረመኔዎች ነን" -[ቶማስ ኤዲሰን]***

በአንድ የትግል ሂደት ሞራላዊ ወይም ስነ-ምግባራዊ እሴቶች በራሳቸው ለትግሉ የአቅም ግብዓት ሆነው ስለሚያገለግሉ የሞራል ጉዳይን ሙሉ በሙሉ ከስልት ውጤታማነት የተነጠለ አድርጎ ማየት ተገቢ አይሆንም። ይህንን ግምት ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ በጐላ ሁኔታ ከሞራል አኳያ ሰላማዊ ትግልን የበለጠ ተመራጭ የሚያደርጉት ቁም ነገሮች አሉ። እነዚህ ቁም ነገሮች ከአንድ ግለሰብም ሆነ ማህበረሰብ የግል ወይም የቡድን እሴቶች፣ ስነ-ምግባሮችና ህሊናዊ ብያኔዎች የሚመነጩ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህንን ለማለት የሚያስችሉንን የሞራል ጥያቄዎች በቅድሚያ ለማየት እንሞክር።

### *አንደኛ፡*

ለአገራችን አጠቃላይ ኋላ ቀርነት አንዱና ዋነኛ ምክንያት የሰላም ዕጦት ነው። ከዚህ አኳያ የትግላችን ዋና ግብና ውጤት ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን ሊሆን ይገባል። ስለዚህ ይህንን የምንታገልለትን ግብ፣ ከግቡ ተፃራሪ በሆነ የኃይል አማራጭ ለማሳካት መሞከር ተገቢ አይሆንም። ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም ሰላምን እየተመኘን፣ ነገር ግን ሰላምን አጥተን የኖርነው ሰላምን ከጦርነት ለማዋለድ ከመሞከር አዙሪት መውጣት ባለመቻላችን ነው። ስለሆነም የትግላችን ትርጉምና ውጤታማነት በዋናነት "የትም ፍጭው ዱቄቱን አምጭው" ከሚለው የአገራችን ማኪያቬሊያዊ የሆነ አውዳሚ አመለካከት በተፃራሪ ሰላማዊ የትግል ስልትን በፅናት ማካሄድ በመቻላችንና ለዚህ ስልት በምናበረክተው አስተዋፅኦ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

በሰላማዊ ትግል ፅኑ እምንት ያላቸው ሰዎች የሰው ልጅ ህይወት ውጤታማነት ላይ ያላቸው ፍልስፍና "ያመኑበትን እያደረጉ መኖር" የሚል ስለሆነ ሰላማዊ ትግልን የማይቀየር ቋሚ ምርጫቸው አድርገው ያያሉ። ለዚህም ነው "የሂደቱ ፍትሃዊነት የግቡን ውጤታማነት ያረጋግጣል" የሚለው የዘመኑ የሰላማዊ ትግል አንኳር መርህ በስፋት ተቀባይነት ያገኘው።

ታላቁ ሳይንቲስት አልበርት አነስታይን ስለ ኃይል አማራጭ ያለውን አሉታዊ አመለካከት ሲገልፅ "የዚህ ዓይነቱ አስከፊ ተግባር ተሣታፊ ከምሆን አካሌ ተቆራርጦ ቢጣል እመርጣለሁ" ያለው ያለምክንያት አይደለም። የሞራል ጥያቄ የህይወት ዋጋ ጭምር ሊከፈልለት የሚገባ ታላቅ የሰው ልጆች እሴት በመሆኑ ነው።

## *ሁለተኛ፡*

ከሞራል ወይም ከመርህ ጋር በተያያዘ ሌላው ሰላማዊ ትግልን እንድንደግፍ የሚያደርገን ምክንያት እኛ ዋጋ ልንከፍልለት የማንፈልገውን ወይም የማንችለውን የኃይል አማራጭ ማሞካሸትም ሆነ መስበክ ከሞራል አኳያ የማይገባ መሆኑ ነው። ሰላማዊ ትግልን የሞራል ጥያቄ አድርጎ የሚያየው ጋንዲ ***"እኔ ራሴ ስለማላምንበት ኃይል-ተኮር ስለሆነ አማራጭ ስልት ላስተምርህ አልችልም። እኔ የማስተምርህ የህይወት ዋጋ የሚያስከፍልህም እንኳ ቢሆን ለማንም አንገትህን እንዳትደፋ ብቻ ነው"*** በማለት የተናገረው ለሞራል መጠበቅ ቁርጠኛ አቋም ስላለው ነው።

የኃይል ወይም የትጥቅ ትግል ውድና ምትክ የሌለውን የሰው ልጅ ህይወት በመግደልም ሆነ በመሞት መስዋዕት ማድረግን ይጠይቃል።ስለዚህ ይህንን ስልት ደግፎ ለመቆም ወይም ሌሎች እንዲሳተፉበት ለመቀስቀስ ሁለት ከሞራል ጋር የተያያዙ ቅድመ-ሁኔታዎች መሟላት ይኖርባቸዋል።

የመጀመሪያው በስልቱ ተገቢነትና ውጤታማነት ማመን ሲሆን፣ ሁለተኛው ስልቱ የሚጠይቀውን መስዋዕትነት ለመክፈል ፈቃደኛና ዝግጁ መሆን ነው። ሁለቱንም ተያያዥ መስፈርቶች የማናሟላ ሰዎች የኃይል አማራጭ ደጋፊም ሆነ ሰባኪ ለመሆን የሚከለክለን ህግ ላይኖር ቢችልም ከሞራል አኳያ ግን ዳር ቁመን የጦርነት ቀስቃሽ መሆን ተገቢነት የለውም። ምክኒያቱም የኃይል ወይም የጦርነት አማራጭ ለመግደልም ሆነ ለመሞት መወሰንን የሚጠይቅ ስልት ስለሆነ ከሞራል፣ ከህግም ሆነ ከሃይማኖት አኳያ "ሰው ሰውን እንዴት ይገድላል? ማንስ ለማን ሊሞት ይገባል?" የሚሉ ፈታኝ ጥያቄዎችን ማስነሳቱ አይቀሬ ይሆናል። በአንፃሩ ሰላማዊ የትግል ስልት ግን ራስን ለመሞት ከማዘጋጀት ባለፈ ሌሎችን በመግደል በሚመጣ ለውጥ የማያምን ስለሆነ የሞራል ጥያቄ አይነሳበትም። እንዲያውም የሞራል የበላይነትን ሊያጐናፅፍ ይችላል።

ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የትጥቅ ትግልን የሚመርጡ ሰዎች የቱንም ያህል የሚከተሉት ስልት ስህተት ነው ብለን ብናምንም የቆሙለት ዓላማ ህዝባዊ ከሆነና ለዚያ ዓላማም የህይወት መስዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ሆነው በጦር ሜዳ ከተሰለፉ ግን ቢያንስ ለሚያምኑበት ዓላማ የማይተካ ውድ ህይወታቸውን ለመሰዋት በመወሰናቸው ተገቢ አክብሮት ልንሰጣቸው ይገባል። የመረጡትን ስልት ስንቃወምና ስንተች በዚያው መጠን ላመኑበት ህዝባዊ ዓላማ ለመሞት ስለወሰኑት ከባድ ውሣኔ ተገቢውን አክብሮት መስጠት ይገባናል።

ነገር ግን ራሳቸውን በተመቸ ቦታ ላይ በርቀት አስቀምጠው የእርስ-በርስ ጦርነትን "ግፋ በለው" ለሚሉ፣ "ምነው ድል ለማድረግ ዘገያችሁ?" በማለት ተዋጊዎችን በምሬት ለሚወቅሱ፣ "ከድል በፊት ለድርድር እንዳትቀመጡ" በማለት በተዋጊዎች ላይ ጫና ለሚፈጥሩ፣ ፊታቸው በሳቅና በደስታ ስሜት ተሞልቶ ስለጦር ሜዳ ውሎ ትንታኔና ዜና ለሚያቀርቡ ሰዎች ግን አክብሮትም ሆነ አድናቆት ሊኖረን አይገባም። የእርስ-በርስ ጦርነትን ተገደንና ምርጫ አጥተን ከገባንበትም እያዘንን እና

እየተቆጨን የምናካሂደው እንጂ እንደ መዝናኛ ጨዋታ በሳቅና በደስታ የምንፈፅመው ተግባር ሊሆን አይገባም። ምክንያቱም በእርስ-በርስ ጦርነት መደሰት ጤናማ አመለካከት ሊሆን አይችልም።

### *ሦስተኛ:*

የዜጐችና የህብረተሰብ "ደህንነት"ወይም "ጤንነት" ጉዳይ ሌላው ሰላማዊ የትግል ስልትን ከሞራል አኳያ እንድንደግፍ የሚያደርገን ምክንያት ነው። ስለ ጦርነት አዙሪት መቀጠል ስናስብ ትልቁ አስጨናቂ ጥያቄ "ለዘላቂ ውጤት ለማያበቃ ጦርነት የስንት ሺህ ወይም ሚሊዮን ሰዎችን ህይወት መገበር አለብን?" የሚለው ቢሆንም ከሞራል አኳያ የህብረተሰብ "ጤንነት" ጉዳይም ሌላው ሊያሳስበን የሚገባ ቁም ነገር ነው።

ለአንድ ህዝብ በድህነት እንደመኖር አስከፊ ፈተና የለም። በድህነት ላይ ጦርነት ሲጨመር ግን ህዝቡ በመሰረታዊ የቁስ ፍላጐት እጦት ብቻ ሳይሆን በስነ-ልቦና መቃወስ ጭምር ጤናው የሚታወክና የሚሰቃይ ይሆናል። አንድ ህዝብ ከአንድ ጦርነት ወደ ሌላ ጦርነት ያለምንም የፈውስ ሂደት በተሸጋጋሪ ቁጥር ለድህረ የስነ-ልቦና ቀውስ /Post Traumatic Effect/ እንደሚጋለጥ በመስኩ የተካሄዱ በርካታ ጥናቶች ያሳያሉ።

በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በጦርነት ሂደት ውስጥ ባለፉ ዜጐችና የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚፈጠር አሉታዊ ውጤትና ዘላቂ ጉዳት ይኖራል። "አብረን ሰው እንሁን" የሚለውን በሰላምና በግጭት ዙሪያ ትኩረት ያደረገ ጥሩ መጽሐፍ ያበረከተልን ፓስተር ሰለሞን ጥላሁን እንደሚለው ጦርነትን ተከትሎ የሚመጣን ስነ-ልቦናዊ ስብራትና ቁስል የሚያሽር የፈውስ ሂደት እስካልተካሄደ ድረስ ህብረተሰብ በዘፈቀደና በቀላሉ ወደ ጤናማና ሰላማዊ ሁኔታ ሊሸጋገር አይችልም። በእንዲህ ዓይነቱ ስነ-ልቦናዊ ህመም የሚጠቃው ወገንም በጦርነቱ ሂደት የተሸነፈው ወይም አካላዊ ጉዳት የደረሰበት ብቻ ሳይሆን "አሸናፊ ነኝ" የሚለው ወገንም የተመሳሳይ ህመም ሰለባ ከመሆን አይድንም።

"በጦርነት የኖሩ በጦርነት ያልቃሉ" የሚለው አባባል ያለምክንያት የሚነገር አይደለም። ጦርነት ሁልጊዜም ቂጣን፣ ፍርሃትን፣ ጥላቻንና በቀልን ተከትሎ የሚመጣ ክስተት በመሆኑ ተጠቂና ተሸናፊ የሆነውን ወገን ብቻ ሳይሆን አጥቂና አሸናፊ ናቸው የሚባሉትን ወገኖች ጭምር ጐድቶ የሚያልፍ ነው። ተዋቂዋ የሚዲያ ሰው ኦፕራ ዊንፍሬይ "በቅድሚያ ራስህን ሳትጠላ ሌሎችን ልትጠላ አትችልም"፣ ስፔናዊው አንቶኒዮ ፍራጓስ "የኃይል ድርጊት የሌሎችንሃሳብ ከመፍራትና ስለ ራስ ያነሰ እምነት ከመኖር የሚመነጭ ነው"፣ ታዋቂው ፀሐፊ ኤሪክ ሆፈር "በሌሎች ላይ ጨካኝና ምህረት የለሽ የምንሆነው አስቀድመን ራሳችንን ስንክድ ነው" ያሉት የኃይል አማራጭ ምንጩ ችግር፣ የመጨረሻ ውጤቱም ችግር መሆኑንና የግጭት ሂደትም ሁሉንም ወገን ጐድቶ የሚያልፍ አደገኛ ክስተት መሆኑን በመረዳት ነው።

የጅምላ አስተሳሰብንና የመንጋ ንቅናቄን /Mass Movement/ በመተቸት ከዛሬ 70 ዓመት በፊት "እውነተኛ አማኞች" /The True Believers/ የሚለውን እውቅ መፅሐፍ የፃፈው ኤሪክ ሆፈር "አክራሪ በሆነ ትግል ነፃነትን ለማግኘት የሚታገሉ ሰዎች ነፃ በሆነ ማህበረሰብ ውስጥም ለመኖር የሚቸገሩ ናቸው" ይላል። ይህንን በማለትም ሳያበቃ "አክራሪዎች የሚያጠፉት ሌላ ጠላት ካጡ እርስ-በርሳቸውም ቢሆን ይጠፋፉሉ" በማለት የኃይል አማራጭ ከህብረተሰብ ጤና አኳያ ያለበትን መሰረታዊ ድክመት ለማሳየት ሞክሯል።

ኢትዮጵያውያን ሁልጊዜም እየተዋጋን፣ ሁልጊዜም ለችግራችን መፍትሄ ርቆን የኖረው በዋናነት ከጦርነት አዙሪት መላቀቅ ባለመቻላችን ነው። ስለሆነም ይህች አገር የዘመናት ስብራቷና ቁስሏ በዘላቂነት እንዲድን ከተፈለገ ሰላማዊ ትግልን መደገፍና ጦርነትን መቃወም ከህብረተሰብ ደህንነት ጋር የተያያዘ የሞራል ግዴታችን ሊሆን ይገባል።

### አራተኛ:

ሌላው ከሰላማዊ የትግል ስልት ጋር ተያይዞ የሚነሳው የሞራል ጥያቄ የህጋዊነት ጉዳይ ነው። የሰውን ልጅ ከሌሎች እንስሶች በዋናነት የሚለየው የህግ ተገዥ መሆኑ ነው። ለአንድ አገር እና ህዝብ የህግ የበላይነት መከበርና መኖር ታላቅ የደህንነት ዋስትና ነው። ጦርነት የራሱ ህግ ቢኖረውም በአንፃራዊነት ሰላማዊ ትግል ከትጥቅ ትግል ይልቅ ለህጋዊነት የሚቀርብ ስልት በመሆኑ ከሞራል አኳያ የበለጠ ተመራጭ ነው። በተለይም በአንድ አገር ውስጥ በዜጎችና በመንግስት መካከል በሚካሄድ ትግል (የአገሩ ህግ ሰላማዊ ትግልን በህጋዊነት የተቀበለ ሆኖ ከተገኘ) ሰላማዊ ታጋዮች ህጋዊ ሲሆኑ ከዚያ በተቃራኒው ሰላማዊ ታጋዮችን የሚያፍነው፣ የሚያስረውና የሚገድለው አገዛዝ ግን ህገ-ወጥ ይሆናል። ስለሆነም በእንዲህ ዓይነቱ ነባራዊ ሁኔታ ውስጥ በምትገኘው አገራችን ህግን አክብሮ የሚካሄድ ሰላማዊ ትግል በሞራል የበላይነት ጭምር ታግዞ ለአሸናፊነት የመብቃት የተሻለ ዕድል ይኖረዋል።

## 2.2. ሰላማዊ ትግል ከስልት አዋጭነት /Strategy/ አኳያ

**"ከኃይል-ተኮር አማራጭ ጋር ሲነፃፀር ሰላማዊ ትግል ከአስር እጥፍ በላይ ወደ ዲሞክራሲ የማሸጋገር ዕድል አለው"** - *[ኤሪካ ቸኖዌዝ]*

ሞራል ራሱን ችሎ ትልቅ ፋይዳ ያለው ቁም-ነገር ቢሆንም ከፖለቲካ ትግል ስልት ምርጫ አኳያ ግን ውጤታማነትን ቀዳሚ መመዘኛ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ሁሉም ነገር አንፃራዊ ነውና "ሰላማዊ ትግል ምን ያህል ተገቢና አዋጭ ነው?" የሚለው ጥያቄ መመለስ ያለበት ከርሱ በተቃራኒ ካለው ኃይል-ተኮር ስልት ጋር ተነፃፅሮ ነው።

ከኃይል-ተኮር የትግል ስልት በተነፃፃሪ ሰላማዊ የትግል ስልት የበለጠ ተመራጭና አዋጭ ስለመሆኑ ከአከራካሪነት ያለፈ እውነታ ሆኗል። የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጥቅምት 2 ቀን "የሰላማዊ የትግል ስልት ቀን" ሆኖ እንዲከበር ያደረገውም ያለምክንያት ሳይሆን ስልቱ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ሰፊ ተቀባይነት ያገኘ በመሆኑ ነው። ከዓለም አቀፍ ሽልማቶች ሁሉ በቀዳሚነት ትኩረት የሚሰጠው የሰላም የኖቤል ተሸላሚነት የሆነውም ሰላማዊ ትግል ለዓለም ሰላም ያለው ፋይዳ እጅግ ከፍተኛ መሆኑ ተቀባይነት ስላገኘና የዘመናችን የጀግንነት ትርጉም በጦርነት ሳይሆን በሰላም አርበኝነት የሚገለፅ በመሆኑ ነው።

በወርልድ ፖፑሌሽን ሪቪው ዘገባ መሰረት (አነስተኛና ዓለም-አቀፍ ግጭቶችን ሳይጨምር) በዓለም ላይ በአሁኑ ወቅት "የእርስ በርስ" በሚባል ደረጃ ጦርነት እየተካሄደባቸው የሚገኙ አገሮች ቁጥር ኢትዮጵያን ጨምሮ ከ8 ወይም ከ5 በመቶ ያልበለጠ ነው። ይህ የሚያሳየውም አብዛኛው የዓለም ህዝብ ጦርነት ራሱ ችግር እንጂ የችግር መፍቻ መሣሪያ እንዳልሆነ አምኖ የተቀበለ መሆኑን ነው። ነገር ግን አገሩ ኢትዮጵያ፣ እኛም ኢትዮጵያዊያን ነንና ዛሬም ላይ ሆነን "ሰላማዊ ትግል ይጠቅማል ወይም አይጠቅምም?" ብለን ለመከራከር ተገደናል።

የሰላማዊ ትግልን ስልት ውጤታማነት በአግባቡ ለመለካት የተወሰኑ ግልፅነት ያላቸው መመዘኛዎች ያስፈልጉናል። "ከታሪካዊ ሂደት አኳያ ሰላማዊ የትግል ስልት ከየት ወደ የት እየሄደ ነው? ሰላማዊ ትግል ከሚጠይቀው ጊዜ፣ ከሚጠይቀው ሰብዓዊና ቁሳዊ መስዋዕትነት፣ ከሚያስገኘው ዘላቂ ጥቅም አኳያ ውጤታማነቱ እንዴት ይታያል?" የሚሉትን ጥያቄዎች ዘርዘር አድርጎ እንደሚከተለው ማየት ይጠቅማል።

## 2.2.1. ሰላማዊ ትግል ከታሪካዊ ሂደት አኳያ

***"ጠላቶቻችሁን ውደዱ" - መጽሐፍ ቅዱስ***

የታሪክና የሃይማኖት መዛግብቶች እንደሚያሳዩት ሰላማዊ ትግል እንደ አንድ ስልት ጥቅም ላይ መዋል የጀመረው ከጥንታዊ የቻይና፣ የግሪክና የሮማውያን ዘመን ጀምሮ ነው። በተለያዩ ጥንታዊ ሃይማኖታዊና ባህላዊ እሳቤዎችም ከፍተኛ ቦታ ያለው ስልት ነው። የተግባር ተቀባይነቱ እምብዛም ቢሆንም "አትግደል!" የሚለው የኦሪት ዘመን ህግ፣ "ጠላቶቻችሁን ውደዱ" የሚለው የአዲስ ኪዳን ህግ የሚያሳየን ሰላማዊነት ምን ያህል ጥንታዊ ተቀባይነት ያለው እሳቤ መሆኑን ነው።

ከፖለቲካ የስልጣን ጥያቄ ጋር በተያያዘ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ድረስ የሰላማዊ ትግል አድገት እጅግ አዝጋሚ የነበረ ቢሆንም ከ1765 እስከ 1775 ድረስ አሜሪካኖች ከእንግሊዝ ቅኝ-ግዛት ነፃ ለመውጣት፣ ከ1850 እስከ 1867 ሃንጋሪ ከአውስትሪያ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት፣ በ1905 ሩሲያን ከዛሩ አገዛዝ ነፃ ለመውጣት፣ ከ1913 እስከ 1919 ድረስ በአሜሪካ ለሴቶች የምርጫ መብት መከበር፣ እንደገና ከ1917 ጀምሮ ደግሞ የሩሲያን አብዮት ለማቀጣጠል በተደረገው ትግል ሰላማዊ የትግል ስልት በአንፃራዊነት በሰፊው ጥቅም ላይ ውሏል።

ዓለማችን የአንደኛውን የዓለም ጦርነት ካስተናገደች በኋላም የጦርነት አስከፊነትና የሰላማዊ ትግል አስፈላጊነት የበለጠ ተቀባይነት እያገኘ በመምጣቱ ከ1918 በኋላ የሰላም ጥናት ተቋማት በዓለም ላይ በፍጥነት መስፋፋት ጀምረዋል። ከ1930 የጋንዲ "የጨው ዘመቻ /Salt March/" ጀምሮም በርካታ በቅኝ-ግዛት ስር የነበሩ አገሮችም ሰላማዊ ትግልን ከሞላ ጐደል ተጠቅመውበታል። ከሁሉም በላይ ከቀዝቃዛው የዓለም ጦርነት ማክተም በኋላ አብዛኛዎቹ የምስራቅ አውሮፓና ሌሎች የሶሻሊስት ርዕዮት አራማጅ የነበሩ አገሮች ወደ ዴሞክራሲ ለመሸጋገር ስልቱን በስፋት ተጠቅመውበታል። ከዚያም በላይ ሰርቢያን፣ ዩክሬይንን፣ ኤልሳልቫዶርን፣ ጓቲማላን፣ ፊሊፕንስን፣ ማይናማርን እና ስሪላንካን የመሳሰሉ አገሮች ሰላማዊ ትግልን አምባገነናዊ ስርዓቶችን ለመጣል ተጠቅመውበታል።

ከ2010 ጀምሮ የአረብ ስፕሪንግ አብዮት በተካሄደባቸው አገሮችም ሰላማዊ ትግል ቢያንስ አምባገነን መንግስታትን ከስልጣን በማውረድ ረገድ ያለውን ከፍተኛ አቅም አሳይቷል። በአጠቃላይም በፍሪደም ሃውስ ሪፖርት መሰረት ባለፉት 50 ዓመታት በሰላማዊ ትግል ወደ ዴሞክራሲ የተሸጋገሩ አገሮች ቁጥር በእጥፉ አድጓል።

በአገራችን ሰላማዊ ትግል በበቂ መጠን ስራ ላይ የዋለበት ወቅት ባይኖርም በተሻለ ሁኔታ በተሞከረባቸው ወቅቶች ግን ቀላል የማይባል ለውጥ ማምጣት ችሏል። ለ40 ዓመታት በስልጣን ላይ የነበረው የአፄ ኃይለስላሴ ንጉሳዊ ስርዓት የተገረሰሰው በዋናነት የአገሪቱ ተማሪዎችና የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ባካሄዱት ያልተደራጀ ሰላማዊ ትግል ነው። ወታደራዊው የደርግ መንግሥት የወቅቱን የሰላማዊ ትግል ጅማሮ በቀይ ሽብር የጭካኔ እርምጃ እንዲዳፈን ቢያደርገውም 1983 ዓ.ም. ላይ ኢህአዴግ ለስልጣን ሲበቃ ሰላማዊ ትግል ህጋዊ እውቅና ያገኘ ስልት ለመሆን በቅቷል። በጅማሮ ደረጃ የነበረው ሰላማዊ ትግል በብዙ አፈናና ጫና ውስጥም ሆኖ በ1992 ዓ.ም. እና በ1997 ዓ.ም. በአገሪቱ በተካሄዱት ምርጫዎች ቀላል የማይባሉ ለውጦችን የማምጣት አቅምና ተስፋ እንዳለው አሳይቷል።

በ27 ዓመቱ የኢህአዴግ ዘመን ሰላማዊ ትግሉ በፈጠረው ጫና አገዛዙ ተገዶና ለህልውናው ስጋት አድሮበት አንዳንድ የህዝብ ጥያቄዎችን ለመቀበልና ቀላል የማይባሉ የልማት ሥራዎችን ለመሥራት ሲገደድ ታይቷል። በመጨረሻም 2010 ላይ በተካሄደው አንፃራዊ የሰላማዊ ትግል እንቅስቃሴ አገዛዙ ተገዶ ከውስጡ ሊፈረካከስና ለጊዜውም ቢሆን የህዝቡን የለውጥ ጥያቄ ተቀብያለሁ ለማለት ችሏል። በአጠቃላይ ሰላማዊ የትግል ስልት በታሪክ ሂደት ያሳየው ለውጥ አዳጊና ወደ ኋላ ሊመለስ በማይችል

መጠን ሰፊ ተቀባይነት እያገኘ የመጣ ነው። ለዚህም ነው ገና ከዛሬ 80 ዓመታት በፊት የሰላማዊ ትግልንእምቅ አቅም የተገነዘበው ማሃትማ ጋንዲ “ሰላማዊ ትግል በሰው ልጅ እጅ ውስጥ የሚገኝና በተፈለገ ጊዜ ሥራ ላይ ሊውል የሚችል ታላቅ ኃይል ነው” በማለት የተናገረው።

## 2.2.2. የሰላማዊ ትግል ውጤታማነት ከፍጥነት፣ ከመስዋዕትነትና ከዘላቂነት አኳያ

*“የምንመኘው ዴሞክራሲያዊ የሆነ ህብረተሰብ መፍጠር ከሆነ፣ ዴሞክራሲ የትግላችን መሳሪያም መድረሻም መሆን አለበት” - [ባያርድ ረስቲን]*

ሰላማዊ ትግል ጥንታዊነት ያለው ስልት ቢሆንም የመገናኛ መሠረተ-ልማት ባልተስፋፋበት፣ የነቃ ማህበረሰብና የግል ሃብት በስፋት ባልነበረበት ዘመን የነበረው ጉዞ እጅግ አዝጋሚ ነበር። በአሁኑ **የሉላዊነትና** የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ግን በከፍተኛ ፍጥነት ውጤት ለማምጣት የሚችልበት ወቅት ላይ ደርሷል። በተለይም የመረጃ ልውውጥ ፍሰት የሉዓላዊነት ድንበር የማያግደው ወጅብ በሆነበትና ዜጐች ሬዲዮና ጋዜጣን መጠቀም ሳያስፈልጋቸው የፈለጉትን መረጃ የትኛውም ቦታ ላይ ሆነው ለሚሊዮኖች ማሰራጨት በሚችሉበት በአሁኑ የማህበራዊ ሚዲያ ዘመን፣ ሰላማዊ ትግል እጅግ ባጠረ ፍጥነት ለውጥ የሚያመጣበት ዕድል አግኝቷል። በዚህም ምክንያት ሰላማዊ ትግል ከጦርነት በላይ ለአምባገነናዊ አገዛዞች የስጋት ምንጭ ሆኗል።

ለምሳሌ ከ13 ዓመት በፊት በተካሄደው የአረብ ስፕሪንግ አብዮት ወቅት በቱኒዚያ የተካሄደው አመፅ መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ የወሰደበት ጊዜ ከአንድ ወር ያነሰ ነበር። የግብፅ አብዮት ሆስኒ ሙባረክን ከስልጣን ለማውረድ የወሰደበት ጊዜ ደግሞ 18 ቀናት ብቻ ነው። የቅርቡ የስሪላንካ ሰላማዊ አመፅም መንግስትን ከስልጣን አባሮ ቤተ መንግስቱን ለመቆጣጠር የወሰደበት ጊዜ አራት ወር ብቻ ነው። በአንጻሩ የጠመንጃ ትግል የተቀላቀለበት የሊቢያ አመፅ ግን ኮሎኔል ጋዳፊን ከስልጣን ለማውረድ የፈጀበት ጊዜ ስምንት ወራት አካባቢ ሲሆን በተመሳሳይ የየመን አብዮትም ፕሬዚዳንት አሊ አብዱላህ ሳላህን ከስልጣን ለማውረድ የፈጀበት ጊዜ አሥራ አንድ ወር ነው።

በአረብ ስፕሪንግ አብዮት ወቅት በሰላማዊ መንገድ ብቻ የተካሄዱት አመፆች በአጭር ጊዜ ለውጥ ያመጡ ሲሆን፣ ከጠብመንጃ አመፅ ጋር የተቀላቀሉት ግን በአንፃራዊነት ረዥም ጊዜ ሲቆዩ ታይቷል። እንዲያውም በዚያው በአረብ ስፕሪንግ አብዮት ወቅት በሶሪያ የተጀመረውና፣ ከጅምሩ ወደ ጦርነት የተቀየረው እንቅስቃሴ ለዓመታት የተራዘመ አውዳሚ ጦርነት ከማስከተሉም በላይ መንግስትን ከስልጣን ማውረድ ሳይችል ቀርቷል።

በአራት ወር ሰላማዊ ትግል በቅርቡ መንግስት ከስልጣን በወረደባት በሲሪላንካም ከ30 ዓመት በላይ የትጥቅ ትግል ያካሄደው የታይሚል ታይገር አማፂ ኃይል በመንግስት ተደምስሶ ህልውናው አክትሟል። ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ባልተደራጀና ባልተቀናጀ ሁኔታም ቢሆን የሚካሄዱ ሰላማዊ ትግሎች መንግስትን ከስልጣን ከማውረድ አኳያ በአጭር ጊዜ ለውጥ የማምጣት ብቃት እያገኙ መሆኑን ነው።

የአንድ ትግል ዋናና የመጨረሻ ግብ የሰው ልጆችን ደህንነት ማስጠበቅ ስለሆነ የአንድን ትግል ውጤታማነት በዋናነት በትግሉ ሂደት ከሚከፈለው መስዋእትነት አንፃር አያይዞ መመዘን ተገቢ ይሆናል። አከራካሪ ባልሆነ መጠን መረጃዎች የሚያሳዩት ከሰላማዊ ትግል ይልቅ ኃይል-ተኮር የትግል ስልቶች በብዙ እጥፍ መስዋዕትነት የሚያስከፍሉ መሆኑን ነው። ከማህበራዊ ትስስር መበጣጠስና ከኢኮኖሚ ውድመት ጋር በተያያዘ የሚከፈለውን ከፍተኛ ዋጋ ወደ ጐን ትተን ውድና ምትክ የለሽ

ከሆነው የሰው ልጅ ህይወት አኳያ ብቻ ጉዳዩን ብንመዝነው በሁለቱ ስልቶች መካከል ያለው ልዩነት ከተነፃፃሪነት በእጅጉ በራቀ መጠን ሰፊ ነው።

በአገራችን ዘመናዊ የፖለቲካ ሂደት ተጀምሯል ተብሎ ከሚታመንበት ከ1953 ዓ.ም. እስከ ንጉሱ መውደቅ ድረስ ለ14 ዓመታት በተካሄደው የተማሪዎችና የወጣቶች ሰላማዊ ትግል የሞቱት ወጣቶች ቁጥር በከፍተኛ ግምት (በጥናት የተደገፈ መረጃ ባላገኝም) ከአንድ መቶ በላይ አይሆንም።

ደርግ ስልጣን ይዞ የነጭና ቀይ ሽብር የኃይል ጥቃት ሲጀምር ግን ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በ10ሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ህይወታቸውን አጥተዋል። ለ17 ዓመታት በአገሪቱ በተካሄደው የትጥቅ ትግልም ከመንግስት፣ ከኢህአዴግና ከሻዕቢያ በኩል በድምሩ ከ400 ሺህ በላይ ህዝብ እንዳለቀ ይገመታል። በጦርነቱ ምክንያት ተገቢ ትኩረት አጥተው በረሃብ ህይወታቸውን ያጡት ዜጎቻችን ቁጥርም ከ1 ሚሊዮን በላይ ነው።

ኢህአዴግ ለስልጣን ከበቃ በኋላ እስካሁን ድረስ በተካሄደው ሰላማዊ ትግልም ተመሳሳይ ውጤት ነው የታየው። ለ27 ዓመት በአገሪቱ በተካሄደው ሰላማዊ ትግል ሞተዋል ተብለው የሚገመቱት ዜጎች ቁጥር ከ7ሺህ ያልበለጠ ነው። ጠ/ሚ ዐቢይ ለስልጣን ከበቁ በኋላ ላለፉት 6 ዓመታት በአገሪቱ በተካሄደው የእርስ-በርስ ጦርነት ህይወታቸውን ያጡ ዜጎች ቁጥር ግን በሚሊዮን የሚቆጠር ሆኗል። ለሁለት ዓመት በትግራይ በተካሄደው ጦርነት ብቻ ከ1 ሚሊዮን ያላነሰ ህዝብ አልቋል። ለ5 ዓመት በኦሮሚያ፣ አሁን ደግሞ በአማራ ክልል እየተካሄደ ባለው ጦርነትና ጦርነቱን ተከትለው በሚመጡ ሌሎች ችግሮች ጭምር እያለቀ ያለውን ህዝብ ቁጥር በትክክል ብናውቀው በእኛ አገር የተካሄደውን ዕልቂት ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በስተቀር በዓለም የሚመጣጠነው ሌላ እልቂት አይኖርም። ትክክለኛውን መረጃ ማግኘት ባልችልም ጠ/ሚ ዐቢይ ለስልጣን ከበቁ በኋላ ሰላማዊ ትግል ሲያካሄዱ በብዙ 10 ሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች የታፈኑና የታሰሩ ቢሆንም የተገደሉት ዜጎች ቁጥር ግን ቢበዛ ከ100 ያለፈ አይሆንም።

በሌላው ዓለም የሆነውን መለስ ብለን ለማየትም ከሞከርን እውነታው ተመሳሳይ ነው። ለምሳሌ በደቡብ አፍሪካ ከአፓርታይድ ስርዓት ጋር በተካሄው የረዥም ጊዜ ሰላማዊ ትግል ተገድሏል ተብሎ የሚገመተው የህዝብ ቁጥር 21 ሺ አካባቢ ነው። ለረዥም ዓመታት በአሜሪካ በተካሄደው የሲቪል መብት ጥያቄ ትግል በትክክል ሞተዋል ተብለው በስም መጠቀስ የቻሉት ሰዎች ቁጥር ቢበዛ ከ41 ያልበለጠ ነው። ዩክሬይን በተካሄደው "ብርቱካናማ" አብዮት ከመንግስትና ከተቃዋሚዎች ወገን በጥቅሉ የሞተው 121 ሰው ብቻ ነው። ለብዙ አስርት ዓመታት በስልጣን ላይ የቆዩ አምባገነኖችን ከስልጣን ለማባረር ባስቻለው በአረብ ስፕሪንግ አብዮት ወቅት በቱኒዚያ በተካሄደው ሰላማዊ ትግል የሞቱት ሰዎች ቁጥር 129 ብቻ ሲሆን፤ በግብፅ የሞቱት ደግሞ 846 ናቸው። ከአረብ ስፕሪንግ ጋር በተያያዘ በሶሪያ፣ በየመንና በሊቢያ የተጀመረው አመፅ ግን በሰላማዊ መንገድ ከመቀጠል ይልቅ በቀላሉ ወደ ትጥቅ ትግል በመሸጋገሩ አገራቱን ለከፍተኛ ውድመትና ዕልቂት ዳርጓቸዋል።

በሶሪያ በተካሄደው የእርስ-በርስ ጦርነት ብቻ ከ470 ሺህ በላይ ዜጎች አልቀዋል። በተመሳሳይ ሁኔታ በየመን ከ150 ሺህ፣ በሊቢያ ከ25 ሺህ በላይ ዜጎች አልቀዋል። በቅርቡ በሲሪላንካ ለ4 ወራት በተካሄደው ሰላማዊ ትግል የሞቱት ዜጎች ከ30 ያልበለጡ ሲሆኑ፣ ነገር ግን በታሚል ታይገር አማፅያን አማካኝነት በሲሪላንካ ለሶስት አስርት ዓመታት በተካሄደው ጦርነት ከ80 እስከ 100 ሺህ የሚገመት ህዝብ አልቋል። ይህ ሁሉ ህዝብ ሞቶም የአማፂው የታሚል ታይገር የመጨረሻ ዕጣ-ፈንታ መሸነፍና ከምድረ-ገፅ መጥፋት ነው የሆነው።

በጦርነት ወቅት ከሚሞተው የሰው ልጅ በተጨማሪ ከመኖሪያ ቀያቸው ተፈናቅለው የሚሰደዱ፣ ጦርነትን ተከትሎ በሚመጣ ረሃብና በሽታ የሚሞቱ፣ በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ፆታዊ ጥቃት፣ በጦርነቱ ሂደት በሚያልፈው ህዝብ ውስጥ የሚፈጠረውን ስነ-ልቦናዊ ስብራትና ቁስል፣ በአገርና

በህዝብ ሃብትና ንብረት ላይ የሚደርሰውን አጠቃላይ ውድመት ሁሉ ደምረን ስንመዝነው በሰላማዊ ትግልና በኃይል-ተኮር ትግል መካከል ያለው ልዩነት ከተነፃፃሪነት ባለፈ እጅግ የተራራቀ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህ ከመስዋዕትነት አኳያ ሰላማዊ ትግል በብዙ እጥፍ ከኃይል-ተኮር ትግል ይመረጣል።

ሌላውና እጅግ ጠቃሚ የሆነው ማነፃፀሪያ ዘላቂ ውጤታማነት ነው። ከሰላማዊ ትግል በተፃራሪ ከቆመው ኃይል-ተኮር ስልት በተሻለ ብቻ ሳይሆን በተለየ ሁኔታ ሰላማዊ ትግል ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ሰርዓት በማዋለድ ረገድ የበለጠ ውጤታማ እንደሆነ በዘርፉ የተካሄዱ ጥናቶችም ሆኑ የአብዛኛዎቹ አገራት ተጨባጭ እውነታ በአሳማኝ መጠን ያሳያል። በአንፃሩ ኃይል- ተኮር ትግል ወይም ጦርነት በተራዘመ ጊዜና በብዙ መስዋዕትነት በስልጣን ላይ የሚገኝን አንድ አገዛዝ ከስልጣን ከማውረድ አልፎ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በመገንባት ረገድ እዚህ ግባ የሚባል ተሞክሮና ታሪክ የለውም። በአገራችንም በተደጋጋሚ ሲሆን የታየው ይኸው ነው።

የዓለማችን አብዛኛዎቹ አገሮች በሰላማዊ ትግል ወይም በተራዘመ የተሃድሶ ሂደት ነው ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት መሸጋገር የቻሉት። ሰላማዊ ትግል በአንዳንድ አገራዊ ሁኔታዎችና በተለያዩ ምክንያቶች መንግስትን ከስልጣን ለማውረድ አቅም ሲያንሰው ቢታይም ህዝብን ባሳተፈ አግባብ ባልተቋረጠ ሁኔታ ከተካሄደ ግን ቢያንስ አዝጋሚ ተሃድሶአዊ ለውጥ የማምጣት ዕድል አለው። ህዝብን በስፋት ከማሳተፍና በተከታታይነት ከመካሄድም አልፎ በበቂ ዝግጅት፣ በበቂ ጥናት፣ በበቂ አማራጭ መንገድና በተደራጀ ሁኔታ ከተካሄደ ሰላማዊ ትግል አገዛዝን ከስልጣን ከማውረድ ባለፈ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለማምጣት ያለው ዕድል ሰፊ ነው።

ኃይል-ተኮር ትግል ወይም ጦርነት በአንዳንድ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ድንገታዊና ፈጣን፣ ወይም በተራዘመ ሂደት ለውጥ ሲያመጣ ሊታይ ይችላል። ነገር ግን እነዛ ድንገቴ ወይም በአዝጋሚ ሂደት የተገኙ ውጤቶች ጊዜያዊ ለውጥ ከመሆን ባለፈ ውለው የሚያድሩ ለውጦች ሆነው አይገኙም። ይህንን እውነታ በውል በመረዳት ነው ጋንዲ **"ኃይል-ተኮር አማራጭን የምቃወመው በምክንያት ነው። የኃይል አማራጭ ጥሩ ውጤት ያመጣ መስሎ ሲታየን ያ ውጤት ግን የአጭር ጊዜ ብቻ ሆኖ ይቀራል። ዘላቂ ሆኖ የሚቀጥለው የኃይል አማራጭን ተከትሎ የሚመጣው ጉዳት ነው"** በማለት የተናገረው።

በዚህም ሳያበቃ ጋንዲ **"በጦርነት የምትጠላውን ወይም የሚጠላህን ሰው ልትገለው ትችላለህ፤ ጥላቻን ግን ልትገለው አትችልም"** ይላል። የኃይል-ተኮር እንቅስቃሴ ደጋፊ የነበረው የሃርቫርዱ ፕሮፌሰር ቼኖዌዝ ደግሞ ያለፈው አንድ መቶ ዓመት ሂደት ላይ ምርምር ካደረገ በኋላ የነበረውን የቀድሞ አቋም በመቀየር- **"ሰላማዊ ትግል ከኃይል አማራጭ ይልቅ አገሮችን ወደ ዴሞክራሲ ለማሸጋገር ከ10 እጥፍ በላይ የሆነ ዕድል አለው"** ብሏል። በተመሳሳይ ሁኔታ ቪዥን ኦፍ ሂዩማኒቲ **"የሰላማዊ ተቃውሞ ኃያልነት" በሚል ርዕስ በፃፈው ርዕሰ-አንቀፅ "ከኃይል ተኮር አመፅ ይልቅ ሰላማዊ ትግል ከ10 እጥፍ በላይ ወደ ዴሞክራሲ የማሸጋገር ዕድል እንደሚኖረው ይገመታል"** ብሎ ፅፏል።

ሰላማዊ ትግል በዚህ መጠን ዘላቂ ውጤት እንደሚያመጣ በመገንዘብም ነው የሲቭል መብት አክቲቪስት የነበረው ባያርድ ረስቲን- **"ማየት የምንፈልገው ዴሞክራሲያዊ የሆነ ህብረተሰብ ከሆነ ዴሞክራሲ መድረሻችን ብቻ ሳይሆን የመታገያ መሣሪያችንም ሊሆን ይገባል"** ያለው። ለሰላማዊ ትግል ህይወቱን አሳልፎ የሰጠው ማርቲን ሉተር ኪንግም **"ኃይል-ተኮር ስልት ጥላቻን የበለጠ የሚያስፋፋ ነው"** በማለት ተናግሯል።

ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ደምድመን ኃይል ተኮር ስልቶች ሁሉ ምንጊዜም አውዳሚ ናቸው፣ ሰላማዊ ትግል ሁሉ ደግሞ ምንጊዜም ለዘላቂ ውጤት የሚያበቃ ነው ለማለት ባንደፍርም ከዘላቂ ውጤታማነት አኳያ ሰላማዊ ትግል በብዙ እጥፍና አሳማኝ በሆነ መጠን ከኃይል-ተኮር ስልት የተሻለ አዋጭ ስልት

መሆኑን ነው። ለዚህም ነው ሬቤካ አዳምሰን ኃይል-ተኮር ትግል አይጠቅምም ብቻ ሳይሆን- **"ኃይል-ተኮር ትግል አስከትሎት የሚያልፈውን ጉዳት እንደገና ለማስወገድ የአራት ትውልድ ዕድሜ ይጠይቃል"** ያለችው።

በአጠቃላይ ጥናቶችም ሆኑ ተጨባጭ ተሞክሮዎች የሚያሳዩን ሰላማዊ ትግል በየትኛውም መመዘኛ ውጤታማ አለመሆኑን አይደለም። ችግሩ ያለው እኛ ለሰላማዊ ትግል በቂ ፅናት ማጣታችን፣ ሊያስከፍል የሚገባውን መስዋእትነት ለመክፈል ዝግጁ አለመሆናችን፣ ሰላማዊ ትግል በሂደቱ የሚያስገኝልንን ውጤት በአግባቡ ይዘን በፅናት ከማስቀጠል ይልቅ በ1967፣ በ1997 እና በ2010 ዓ.ም. ሲሆን እንደታየው አቋራጭ መንገድ ፍለጋ ወደ ኃይል አማራጭ ለመግባት የምንቋምጥ መሆናችን ላይ ነው።

ከሞራልና ከአዋጭነት መመዘኛዎች አኳያ ሰላማዊ የትግል ስልት ከኃይል-ተኮር ስልት የተሻለና አዋጭ መሆኑን በዚህ መጠን ከተገነዘብን "ታዲያ ለምንድን ነው በእኛ አገር ወቅታዊ ፖለቲካ የሰላማዊ ትግል ስልት አዋጭነት አከራካሪ የሆነው?" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንሞክር።

# 3. በሰላማዊ የትግል ስልት ላይ የሚሰነዘሩ ትችቶች ፋይዳ

**"ትችትን የማስወገጃ መንገድ አንድ ብቻ ነው። ምንም አለመስራት፣ ምንም አለመናገርና ማንም አለመሆን"** - [አርስቶትል]

እንደማንኛውም የትግል ስልት ሰላማዊ ትግልም ሙሉ በሙሉ ከድክመት የፀዳ ሊሆን ስለማይችል በሱም ላይ ትችት መቅረቡ የሚጠበቅ ነው። ክርክሩ "ከኃይል-ተኮር ትግል ይልቅ ሰላማዊ ትግል አዋጭና ውጤታማ ነው" የሚል ነው እንጂ "እንከን-የለሽ ነው" የሚል አይደለም። በተለይም ማንኛውም የትግል ስልት ከሚካሄድበት ወቅትና አገር ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተገናዝቦ መካሄድ ስላለበት ምንጊዜም እየተገመገመና እየተተቸ ጉድለቶቹ ሊሟሉና ሊጠናከር የሚገባው ስልት ነው።

በእኛም አገር ሆነ በሌሎች አገሮች በተደጋጋሚ ሲሆን እንደታየው ሰላማዊ ትግልም በጠራ አጀንዳ፣ በበቂ ዝግጅት፣ በሰፊ የህዝብ ተሳትፎና በተለያዩ አማራጭ ስልቶች በተከታታይነት ካልተካሄደና በጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ካልተመራ በስተቀር እሱም እንደ ትጥቅ ትግል መንግስትን ከመጣል ባለፈ ዘላቂ መፍትሄ ሊያስገኝ አይችልም። ስለዚህ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ እንደማንኛውም ትግል ቋሚ ግምገማ ሊካሄድበትና ትችት ሊቀርብበት ይገባል። ከዚህ አንፃር በሰላማዊ ትግል ስልት ዙሪያ ትችት መቅረቡ ተገቢና የሚጠበቅ ቢሆንም በዚህ ዘመን ሰላማዊ የትግል ስልትን 'የፈሪዎችና የደካሞች ምርጫ፣ ተፈትኖ የወደቀ፣ እንዲሁም አፋኝና አሳሪ መንግስት ባለበት አገር ሊካሄድ የማይችል' አድርጎ ከማየትም ባለፈ ጭራሽም ውጤት የማያመጣና ፈጽሞ የማያስፈልግ አድርጎ ስልቱን ለመቃወም መሞከር ግን ከእውነትና ከዓለም ህዝብ አመለካከት ተፃርሮ መቆም ይሆናል። ከእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ የሚቀርቡትን እነዚህን ትችቶች ጠቅለል ባለ ሁኔታ እንደሚከተለው ለማየት እንሞክር።

## 3.1. ሰላማዊ ትግል በበቂ ሁኔታ ተሞክሮ ወድቋል?

**"ሰላማዊ ትግል መቼም ቢሆን መለወጥ የሌለበትና በጥቃት ፊትም ላይ ሆናችሁ ልትከተሉት የሚገባ ስልት ነው" - [ማሃትማ ጋንዲ]**

ሰላማዊ ትግልን ለመቃወም ተብለው በአሁኑ ወቅት በአገራችን የፖለቲካ መድረክ ከሚቀርቡት ትችቶች ውስጥ አንዱ "ሰላማዊ ትግል በአገራችን በበቂ ሁኔታ ተሞክሮ ወድቋል" የሚል ነው። ይህ ግን ከእውነታው እጅግ በጣም የራቀና የተሳሳተ ትችት ነው። ምክንያቱም ሰላማዊ ትግል በአገራችን እንኳንስ በበቂ ሁኔታ ተሞክሮ ወደቀ ሊባል ይቅርና በበቂ ሁኔታ ተጀምሯል ሊባልም አይችልም።

በመስኩ ጥናት ያደረጉ አንዳንድ ባለሞያዎች ሰላማዊ ትግል ሊካሄድባቸው የሚችል ከ100 በላይ የሆኑ መንገዶች እንዳሉ ይገልፃሉ። አታካች የሆኑትን ዝርዝር ጉዳዮች ትተን በማዕቀፍ ደረጃ ያሉትን ጥቅል የሰላማዊ ትግል ማካሄጃ ስልቶች ለማየት ብንሞክር ከደርዘን በላይ ሆነው እናገኛቸዋለን። ለምሳሌ - ህዝባዊ እምቢተኝነት፣ የአደባባይና የጐዳና ላይ ተቃውሞ፣ የተሳትፎ እቀባ፣ የረሃብ አድማ፣ የሥራ ማቆም አድማ፣ ላልተገቡ ጉዳዮች ትብብርን መንፈግ፣ ባልተገቡ ሂደቶች ላይ ጣልቃ መግባት፣ መግባባትና ማሳመን፣ የመገናኛ ብዙሃን ዘመቻ፣ የዲፕሎማሲ ዘመቻ፣ ህብረተሰብን ማንቃትና ማደራጀት፣ እርቅ መፍጠርና የሰላም ግንባታ፣ ውይይትና ድርድር፣ የምርጫ ተሳትፎ፣ ክስ ማቅረብ፣ የፊርማ ማሰባሰብ ዘመቻ፣ ወዘተ… እና እነዚህን የመሳሰሉ በርካታ መንገዶች አሉ። ከዚህ አኳያ በ27 ዓመቱ የኢህአዴግ ዘመንም ሆነ በአሁኑ የጠ/ሚ ዐቢይ አገዛዝ ወቅት የተሞከረውን ሰላማዊ ትግል ለመመዘን ከሞከርን እንኳንስ ተሞክሮ ወድቋል ሊባልና ተጀምሯልም ሊባል ያስቸግራል። በተለይም በጠ/ሚ ዐቢይ አገዛዝ ዘመን ደካማ በሆነ ሁኔታ ምርጫ ከመሳተፍ፣ ያልተቀናጀና ያልተጠና የመገናኛ ብዙሃን ዘመቻ ከማካሄድና የሰልፍ ፈቃድ ጠይቆ ከመከልከል ባለፈ ሰላማዊ ትግል እዚህ ግባ በሚባል መጠን ገና አልተካሄደም።

በሃይማኖታቸው ላይ የተሞከረን ጣልቃ ገብነት በመቃወም የኦርቶዶክስ ምዕመናን ለተወሰኑ ቀናት ከፈጠሩት ጫና በስተቀር የጠ/ሚ ዐቢይ አገዛዝ እስካሁን ጠንካራ የሰላማዊ ትግል ፈተና አልገጠመውም። ከ3 ዓመት በፊት በአማራ ክልል ከዚያም በቡርጅ፣ በወላይታና በጉራጌ ዞኖች የተካሄዱት ሰላማዊ ሰልፎችም ቀጣይነት እንዲኖራቸው ማድረግ የሚያስችል ጠንካራ የፖለቲካ አመራር በማጣታቸው የትም ሳይደርሱ ቀርተዋል። በተለይም ለሰላማዊ ትግል ዋና ማዕከል መሆን በሚገባት በአዲስ አበባ ከተማ ጠ/ሚ ዐቢይ ለስልጣን ከበቁ በኋላ አንድም የተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ አለመካሄዱ የሚያሳየን ሰላማዊ ትግል የሚገባውን ቦታና ትኩረት አለማግኘቱን ነው። በዚህ አግባብ "ጠይቀን ስለተከለከልን ነው" የሚለው የተቃዋሚዎች ምክንያት በደምሳሳው የራሳቸውን እንጂ የስልቱን ደካማነት አያሳይም።

ከአምባገነናዊ ስርዓት ጋር የሚካሄድ ሰላማዊ ትግል ቀላል አይደለም። በቂ ዝግጅትን፣ በቂ የህዝብ ተሳትፎን፣ ተከታታይነትን፣ በቂ ዕውቀትን፣ የፈጠራ ችሎታን፣ የረዥም ጊዜ ልምድን፣ ከሁሉም በላይ መስዋዕትነት የመክፈል ቁርጠኝነትንና ድፍረትን ይጠይቃል። የጉዳዩ ዋና ባለቤት የሆነውን ህዝብም በሰላማዊ ትግል ስልት ላይ የተሟላ እምነት ኖሮት የትግሉ ቀጥተኛ ተባባሪና ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ ይጠይቃል። ህዝቡ የትግሉ ባለቤት ሆኖ እውቀቱን፣ ጊዜውን፣ ጉልበቱንና ገንዘቡን ከማዋጣት አልፎ ለመታሰርና ለመሞትም ጭምር የሚያስችል ስነ-ልቦናዊ ዝግጅት ከሌለውና እንዲህ ዓይነቱ ትግልም በጠንካራ የተደራጀ ኃይል ካልተመራ በስተቀር ሰላማዊ ትግል በጥቂት ፖለቲከኞች ተዋናይነት ብቻ የትም ሊደርስ አይችልም።

በመስኩ የተካሄዱ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰላማዊ የትግል ስልት ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ ከ3.5% ያላነሰው ህዝብ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የትግሉ ተሳታፊ መሆን አለበት።

ተሳታፊዎቹም የህዝቡን ጥቅምና ፍላጐት በመወከል ረገድ በቂ ብዙሃነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። የሚጠቀሟቸው ስልቶች በዓይነታቸው የበዙና ተከታታይነት ያላቸው፤ ፕሮፓጋንዳዎቹም ጠላትነትን የሚቀንሱና ወዳጅነትን የሚያበዙ መሆን ይገባቸዋል። ከሁሉም በላይ ጫናና ተፅዕኖ ሲበዛባቸው በቀላሉ ወደ ኃይል-ተኮር አማራጭ የማይለወጥ ጠንካር ፅናት ሊኖራቸው ይገባል።

በእነዚህ መሠረታዊ መመዘኛዎች በአገራችን ተካሂዷል የሚባለውን ሰላማዊ ትግል ለመገምገም ከሞከርን እንኳንስ በበቂ መጠን ተሞክሮ ወድቋል ሊባልና ጭራሹኑም ተጀምሯል ሊባል የሚችል አይደለም። ከጅምሩ ሀሞታችን የፈሰሰውና ፈተናውን የወደቅነው በሰላማዊ ትግል እናምናለን የምንለው ፖለቲከኞች ነን እንጂ ሰላማዊ የትግል ስልት አይደለም።

ከፍ ባሉት የዚህ ፅሁፍ ክፍሎች እንዳየነው ሰላማዊ የትግል ስልት ውጤታማነቱ በብዙ አገሮች ከክርክር በላይ በሆነ መጠን የተረጋገጠ ስልት ነው። በእርግጥም ስልቱ ለሌሎች አገሮችና ህዝቦች ሰርቶ እኛ ላይ ሲደርስ ግን የማይሰራ ከሆነ ችግሩ ያለው ከእኛ እንጂ ከስልቱ ሊሆን አይችልም።

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃን ሃቁን በድፍረት መነጋገር ካለብን ድክመቱ የእኛ እንጂ የስልቱ አይደለም። ከትጥቅ ትግል በተለየ በሰላማዊ ትግል ወቅት ቀድመው መስዋእትነት ለመክፈል የሚገደዱት የትግሉ ተከታዮች ሳይሆኑ የትግሉ ግንባር ቀደም መሪዎች ናቸው። በትጥቅ ትግል ወቅት ግን ቀዳሚውን ዋጋ የሚከፍሉት መሪዎች ሳይሆኑ ተከታዮች ናቸው። ከሰላማዊ ትግል ይልቅ የጦርነት መንገድን በዋናነት እየመረጥን ያለነው ፅናት በማጣትና ከዚህ የራስ-ወዳድነት ባህሪ በመነጨ ነው እንጂ ሰላማዊ ትግል ተፈትኖ ስለወደቀ አይደለም። ስለዚህ የራሳችንን ፍርሃትና ቁርጠኝነት ማጣት በሰላማዊ ትግል ድክመት ለማሳበብ መሞከር የተሳሳተ አመለካከት ነው።

## 3.2. ሰላማዊ ትግል አፋኝና ገዳይ መንግስት ባለበት አገር ማካሄድአይቻልምን?

**"የአገዛዞች ምላሽ ኃይል ሲሆን፣ ሰላማዊ ትግል የበለጠ ውጤታማ የመሆን ዕድል አለው"**- [ማሃትማ ጋንዲ]

በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ መድረክ ሰላማዊ የትግል ስልትን ለመቃወም የሚቀርበው ሌላው ምክንያት "የሚያፍን፣ የሚያስርና የሚገድል መንግስት ባለበት አገር ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ አይችልም ወይም አያዋጣም" የሚል ነው።

ከብዙ አገራት ተጨባጭ ሁኔታ ለመረዳት እንደምንችለው ሰላማዊ ትግል አምባገነናዊ መንግስት ባለበትም ሆነ በሌለበት አገር ይካሄዳል። ዴሞክራሲ በሰፈነባቸው አገሮች ብዙውን ጊዜ ሰላማዊ ትግል የሚካሄደው ከፖለቲካ ፓርቲዎች ይልቅ በተለያዩ ማህበራዊ አንቂዎችና የመብት ጥያቄ አቅራቢ በሆኑ ሲቪክ ማህበራት ወይም ቡድኖች ነው። አምባገነናዊ መንግስት ባለባቸው አገሮች ግን ብዙውን ጊዜ ሰላማዊ ትግል የሚካሄደው በፖለቲካ ፓርቲዎች ሲሆን የሚካሄደው ትግልም በዋናነት የሚያተኩረው በስልጣን ጥያቄና በስርዓት ለውጥ ዙሪያ ነው።

ዲሞክራሲያዊ በሆኑ አገሮች የፖለቲካ ፓርቲዎች ብዙውን ጊዜ ለሚያካሂዱት እንቅስቃሴ የሚመጥነው ቃል "ፉክክር"የሚለው ነው እንጂ "ትግል"የሚለው አይደለም።"ትግል"የሚለው ቃል በአንፃራዊነት የሚያሳየው በአፈና፣ በእስራት ወይም በሞት ጭምር ዋጋ መክፈልን ስለሆነ በየ4 ወይም 5 ዓመቱ ከሚካሄድ የምርጫ ፉክክር የተለየና የራቀ ትርጉም ያለው ነው። ስለዚህ ከእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ ስለ ሰላማዊ ትግል ስናወራ በዋናነት ፖለቲካ ፓርቲዎች ለስልጣንና ለስርዓታዊ ለውጥ ስለሚያካሂዱት ትግል እያወራን እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሰላማዊ ትግል መብትን ከሚያፍኑ አምባገነናዊ ስርዓቶች ጋር ብቻ ሳይሆን ከቅኝ-ግዛት ነፃ ለመውጣትና ከአፓርታይድ ስርዓት ለመላቀቅ ጭምር ሊካሄድ ይችላል።በተለይም በአንድ በኩል አምባገነናዊ ስርዓት ባለበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰላማዊ ትግል ማድረግ ለይስሙላም ቢሆን ህጋዊ እውቅና ባገኘበት የኛ ዓይነቱ አገር ሁኔታ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ ህጋዊ ድርጊት ስለሆነ "ሊካሄድ አይችልም ወይም አይገባም" የሚል አሳማኝ ክርክር ሊቀርብበት የሚችል አይደለም። ቢያንስ አገዛዙ በህዝብ ትግል ተገዶ ሰላማዊ ትግል ማድረግን ከአገሪቱ ህግ በአዋጅ እስካልፋቀው ድረስ አፋኝና ገዳይ ስለሆነ ብቻ የሰላማዊ ትግልን አስፈላጊነት ጥያቄ ውስጥ ለማስገባት የሚችል አሳማኝ ምክንያት አይኖርም።

ስለ ሰላማዊ ትግል ትንሽም ቢሆን ግንዛቤ ካለን በብዙ የዓለም አገራት በግልፅና በተደጋጋሚ ሲሆን እንደታየው የፖለቲካ ኃይሎች የሰላማዊ ትግል ማካሄድ የበለጠ የሚገባቸው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ባለበት ሳይሆን አፋኝ የሆነ አምባገነናዊ ስርዓት ባለበት አገር ነው።፡ እውነታው ይህ ባይሆን ኖሮ ጋንዲንና ማንዴላን የመሰሉት ብዙ ዋጋ የከፈሉ ሰዎች የሰላም አርበኞች ሊሆኑ፣ "ሰላማዊ ትግል" የሚባል ፅንሰ-ሃሳብም ከቶውንም ከጅምሩ ሊኖር ባልቻለ ነበር።

እንዲያውም "የሚያፍንና የሚገድል መንግስት ባለበት አገር ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ አይችልም" ከሚለው መከራከሪያበተቃራኒ ስልቱ ከልብ በገባቸው ተጋዮች ዘንድ ሰላማዊ ትግል የበለጠ ውጤታማ ለመሆን የሚችለው አፋኝና ገዳይ መንግስት ሲኖር ነው ተብሎ ይታመናል። ምክንያቱም አፈናና ግድያ የአገዛዙን ባህሪና ማንነት የበለጠ ያጋልጣል፣ ህዝብን የበለጠ በቁጣ ያነሳሳል፣ በመጨረሻም አገዛዙ በህዝብና በዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ዘንድ ቅቡልነት እንዲያጣ ያደርጋል። ይህ ሊከሰት የሚችለው ግን ሰላማዊ ትግል በተከታታይነት በተግባር መካሄድና መኖር ሲችል ነው።

ለዚህም ነው ጋንዲ **"የአገዛዞች ምላሽ ኃይል ሲሆን ሰላማዊ ትግል የበለጠ የመጠናከር ዕድል ይኖረዋል"** ያለው። ጋንዲ ከዚህም በተጨማሪ **"ሰላማዊ ትግል መለወጥ የሌለበት ስልት ነው፤ አደጋ ከፊታችን በተጋረጠበት ወቅትም ጭምር በፅናት ይዘነው ልንቀጥል የሚገባን ስልት ነው"** ያለውም ያለምክንያት ሳይሆን አፈናና ግድያ በሰላማዊ ትግል ወቅት የሚጠበቅ ክስተት መሆኑን ከመገንዘብም በላይ አገዛዙን ለማዳከምና ትግሉን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ፋይዳ እንዳለው በመገንዘቡ ነው።

በእርግጥም እንደ እኛ አስመሳይ /Suedo/ ዴሞክራሲ አለ በሚባልበት አገር አምባገነኖች በጦር ሜዳ ከሚገድሉት 10 ሺህ ታጣቂ ኃይል በላይ በሰላማዊ ትግል የተሰለፉን 10 ሰላማዊ ታጋይ ቢገድሉ የአሥሩ ሰላማዊ ታጋዮች ሞት የበለጠ ትርጉም ይኖረዋል። ምክንያቱም ሰላማዊ ትግል ቢያንስ በህግ ደረጃ በተፈቀደበት ሀገር የመንግስት ግድያ ከህግ፣ ከሞራልም ሆነ ከሰብዓዊነት አኳያ ስህተትና ወንጀል የሚሆነው ሰላማዊ ታጋዮችን ሲገል ነው።

በጦርነት ወቅት ግን መንግስት የጦርነትን ህግ አክብሮ እስከተዋጋ ድረስ ታጣቂዎችን ስለገደለ ብቻ ወንጀለኛ ተብሎ ሊፈረጅ አይችልም። እንዲያውም አሳማኝ የሆነ የፖለቲካ አጀንዳ ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም በአገሪቱ አስመሳይ ህግ መሰረት በወንጀለኛነት ሊፈረጁ የሚችሉት ታጣቂዎቹ ኃይሎች ናቸው። በዚህም ምክንያት ከ10 ሺህ ታጣቂዎች ሞት በላይ የ10 ሰላማዊና ህጋዊ ታጋዮች ሞት የበለጠ ዜና የመሆንና በአገዛዙ ላይም ከፍተኛ የዲፕሎማሲ ጫና የማስከተል አቅም አለው። ለዚህም ነው አገዛዙ ሁልጊዜም ተቃዋሚዎቹን በሰላማዊ ትግል ሳይሆን በጦርነት መግጠምን እየመረጠ ያለው።

ታጣቂ ኃይሎች "ወደ ጦርነት የገባነው በአገዛዙ ህገ-ወጥ ድርጊቶች ተገደን ነው"በማለት የሚያቀርቡት ምክንያት የበለጠ ተቀባይነት ሊኖረው የሚችለውም አገዛዙ ሰላማዊ ታጋዮችን እያፈነና እየገደለ መሆኑ በተግባርና በተጨባጭ ሲታይ ነው። ስለዚህ በሰላማዊ ትግል የሚከፈል መስዋዕትነት ለትጥቅ ትግል ታጋዮች አጀንዳ በማቀበል ጭምር ያለው ፋይዳም ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት

የጦርነት ታጋዮች ለራሳቸው ተቀባይነት ሲሉም ጭምር የሰላማዊ ትግልን መኖር ሊደግፉት እንጂ ሊቃወሙት አይገባም።

ስለዚህ አገዛዙ አፈናና ግድያ ስለሚፈጽም ሰላማዊ ትግል ማካሄድ አይቻልም ወይም አይገባም የሚለው ክርክር ሰላማዊ ትግልን በውል ካለመገንዘብ፣ ወይም ትግሉ መሪዎቹ ላይ ከደቀነው አደጋና መስዋዕትነት ለመሸሽና የራስን ድክመት ለመሸፈን የሚቀርብ ብልጣ-ብልጥነትና ሰበብ ካልሆነ በስተቀር አሳማኝ መከራከሪያ ሊሆን አይችልም።

## 3.3. ሰላማዊ ትግል የደካሞችና የፈሪዎች ምርጫ ነው?

***"ኃይል-ተኮር ስልት የደካሞች የመጨረሻ መደበቂያ ነው"*** *–[ማርቲን ሉተር ኪንግ]*

በወቅቱ የአገራችን ፖለቲካ ሰላማዊ ትግልን የማይቻልና የማያዋጣ ስልት አድርጎ ከማየትም ባለፈ ሰላማዊ ትግልን የሚደግፉና የሚያካሂዱ ሰዎችን ደካሞችና ፈሪዎች አድርጎ ማየት የተለመደ ሆኗል። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ኃይሎች እጅግ ዝቅተኛና ኋላ-ቀር በሆነ የአስተሳሰብ ደረጃ ላይ እንደምንገኝ አንዱ ማሳያ ይህ ይመስለኛል።

ሰላማዊ ትግል በጦርነት እንደሚካሄድ ትግል ተራራና ሜዳን በመቆጣጠርና ነፃ በማውጣት የሚገለፅ አይደለም። ይልቁንም ለትግሉ ደጋፊ እንዲሆን የሚፈለገውን ህዝብ ብቻ ሳይሆን በሌላኛው ወገን የተሰለፉትን ተፎካካሪ ኃይሎች ጭምር በሃሳብ በማሳመንና በማሸነፍ ለውጥ ለማምጣት የሚደረግ ከባድ ትግል ነው። በአጭሩ የሰዎችን አዕምሮ ነፃ የማውጣት ትግል ነው። ስለሆነም በሃሳብ የበላይነት በልጦ በመገኘት አሸናፊ መሆን ጠንካራ የሞራልና የእውቀት የበላይነት ባላቸው እንጂ ደካማና አላዋቂ በሆኑ ሰዎች ሊካሄድ የሚችል ተግባር አይደለም።

ከጀግንነት አኳያ ጉዳዩን እንመዝነው ካልንም ራስን ለመከላከል የሚያስችል ምሽግና ጠብመንጃ ሳይዙ ከገዳዮች ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጦ እንደመታገል የሞራል የበላይነትና ጀግንነት ያለ አይመስለኝም። በዚህም ምክንያት ነው ማርቲን ሉተር ኪንግ **"ኃይል ተኮር ስልት የመጨረሻው የደካሞች መደበቂያ ነው"** በማለት የተናገረው። ፖርቱጋላዊው የሙዚቃ ኮምፖዘር አንቶኒዮ ፍራንሶስ- **"የኃይል ተኮር ስልት ምርጫ የሌሎችን ሃሳብ የመፍራትና ለራስ ያነሰ ግምት ከመኖር የሚመነጭ ነው"** ያለው፣ ከዚህም በላይ ጠበቅ በማድረግ ጋንዲ **"ሰላማዊ ትግል የጀግኖች መሣሪያ ስለሆነ የፈሪዎች መሸሸጊያ መሆን የለበትም"** ያለው። በተጨማሪም አሜሪካዊው የፖለቲካ ሳይንቲስት ጂን ሻርፕ **"ሰላማዊ ትግል የላቀ የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ከፍተኛ አቅም ነው"** ያለው ሰላማዊ ትግል የደካሞችና የፈሪዎች ሳይሆን ከፍተኛ የፈጠራ ችሎታ፣ የሞራል ልዕልና፣ ከፍተኛ የጀግንነትና በራስ የመተማመን ባህሪ ያላቸው ዜጎች ተግባር መሆኑን በመገንዘብ ነው።

ስለዚህ ሰላማዊ ትግልን የደካሞችና የፈሪዎች ምርጫ አድርጎ ለማንኳሰስ መሞከር ከግንዛቤ እጥረት የመነጨ መረዳት እንጂ አሳማኝ ምክንያት ያለው መከራከሪያ አይደለም። ይልቁንም ሰላማዊ ትግል የሰው ልጆች መሠረታዊ እምነትና ዘላቂ መርህ ተደርጎ ሊያዝ የሚገባው ታላቅ የለውጥ መሳሪያ ነው። ለአራት አምባገነን መንግስታት መውደቅ ምክንያት ከሆነውና ራሱን በእሳት በአደባባይ ካቃጠለው ሙሃመድ ቡአዚዝ በላይ የትኛውም የዓለም የጦር ጀነራል እኔ የበለጥኩ ጀግና ነኝ ሊል የሚችል አይመስለኝም።

# 4. በልዩ ሁኔታ ሚዛን የሚደፋ አንድ መከራከሪያ

***"ትጥቅ ትግልን የመረጥነው ወደን ሳይሆን ተገደን ነው" - [የወቅቱ አማጽያን]***

*በዚህ መጣጥፍ ላይ በግልፅ እንዳየነው የሰላማዊ ትግል ስልት ውጤታማነት እንደየአገሩ ተጨባጭ ሁኔታ ይለያያል። ሰላማዊ ትግልን በህግ የከለከሉ አምባገነን መንግስታት ባሉባቸው ሰሜን ኮሪያን፣ ቻይናንና ኤርትራን በመሳሰሉ አገሮች በተለያዩ መንገዶች ሰላማዊ ትግል ሊካሄድ የሚችልበት ዕድል ፈፅሞ የለም ባይባልም በፖለቲካ ድርጅቶች የሚመራና ህጋዊነት ያለው ትግል ማካሄድ ግን አይቻልም። በአንዳንድ አገሮች ልዩ ሁኔታም ሰላማዊ ትግል ማድረግ በህግ የተፈቀደም ሆኖ እያለ ትግሉን በተግባር ለማካሄድ አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። የወቅቱ የኛ አገር ሁኔታም ለአንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎች ወይም የህብረተሰብ ክፍሎች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን እየፈጠረ እንደሆነ እያየን ነው።*

*የጠ/ሚ ዐቢይ አገዛዝ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ በአገራችን ብሄር ተኮር ጥቃት ተበራክቷል። እንዲህ ዓይነቱን ጥቃት የሚፈፅሙት ኃይሎች በግልፅ የሚታወቁና የማይታወቁ ናቸው። መንግስት በዜጎች ላይ የሚደርሰውን እንዲህ ዓይነቱን ማንነት ተኮር ጥቃት መከላከል ያልቻለ ሲሆን፣ መከላከል ካለመቻል አልፎም ለእንዲህ ዓይነቶቹ ወንጀሎች ራሱ ዋና ተዋናይ ወይም ተጠርጣሪ ሲሆን ታይቷል። ለዚህ ዓይነቱ የማንነት ጥቃት ተጋላጭ የሆኑት የህብረተሰብ ክፍሎች ከመንግስት የደህንነት ዋስትና ማግኘት ባለመቻላቸው በራሱ በመንግስትም እየተጠቁ በመሆኑ ታጥቀው ራሳቸውን ለመከላከል ተገደዋል። መንግስትም በአንድ በኩል ዜጎችን ከማንነት ጥቃት የመከላከል ህገ-መንግስተዊ ግዴታውን መወጣት ተስኖት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለማንነት ጥቃት መነሻ ለሆኑት ችግሮች የፖለቲካ መፍትሄ መስጠት አለመቻሉ አላንስ ብሎ በራሳቸው መንገድ ራሳቸውን አስታጥቀው ደህንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚሞክሩትን ዜጎች "ትጥቅ ካልፈታችሁ" በማለት የሚያሳድድበት ሁኔታ ተፈጥሯል።*

*ይህ ከመንግስት ድክመትና ኃላፊነት የጐደለው ተግባር የመነጨ ችግር በርካታ የአገሪቱ ዜጐች ወደው ሳይሆን ተገደውና ተገፍተው ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገቡ አድርጓል። ይህ ክስተትም "በአገሪቱ መካሄድ የሚገባውና ለውጥ ማምጣት የሚያስችለው ሰላማዊ ትግል ነው ወይስ የትጥቅ ትግል?" የሚል ክርክርና ውዝግብ እንዲነሳ አንድ ምክንያት ሆኗል። ለዚህ መጣጥፍ መቅረብ ዋና መነሻ የሆነው ምክንያትም ይኸው ነው።*

*ዜጐች በአሁኑ ወቅት ወደ ትጥቅ ትግል የገቡት ፈቅደውና ወደው ሳይሆን ከፍ ሲል ለመግለፅ በተሞከረው አስገዳጅ ሁኔታ መሆኑ በግልፅ ስለሚታወቅ ለአገሪቱ የሚበጃት ሰላማዊ ትግል ብቻ ነው ብለን የምናምን እኔን መሰል የፖለቲካ ሰዎች እነዚህን ወደ ትጥቅ ትግል የገቡ ወገኖቻችንን መቃወምም ሆነ ማውገዝ የማንችልበት አጣብቂኝ ገጥሞናል። ምክንያቱም ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው እነዚህ ዜጐቻችን ተገፍተው ወደ ትጥቅ ትግል እንዲገቡ ያደረጋቸው በዋናነት የመንግስት ድክመትና ጥፋት በመሆኑ፣ ለችግሩ ሰላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ የመስጠቱ ሰፊ ዕድል ያለውም በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንደሆነ ስለምንገነዘብ የቱንም ያህል የትጥቅ ትግል ለአገራችን የማይጠቅምና ዘላቂ መፍትሄ የማያመጣ መሆኑን ብናምንም የትጥቅ ትግል እያደረጉ ያሉ ኃይሎችን ለማውገዝና ለመቃወም አንችልም፣ አይገባምም።*

*ከላይ በተጠቀሱት የመንግስት ጥፋቶችና ድክመቶች "ወደ ጦርነት የገባነው ወደን ሳይሆን ተገደንና አማራጭ አጥተን ነው" የሚለው የታጣቂ ኃይሎቹ መከራከሪያ ከሞላ ጐደል ከሌሎቹ መከራከሪያዎች በተለየ ምክንያታዊና አሳማኝ ነው። በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ህጋዊ ኃላፊነቱን በማይወጣበት፣ ከዚያም በላይ ራሱ ጥቃት ፈጻሚ በሆነበት ሁኔታ ራስን ከህልውና ጥቃት መከላከል ማንም ሊገድበው*

የማይችል የዜጐች ተፈጥሯዊ መብት ነው። ሰላማዊ ትግል መብት መሆኑ በአዋጅ እስካልተፋቀ ድረስ ማንኛውንም ዓይነት ተፅዕኖ በመቋቋምና በመጋፈጥ ሰላማዊ ትግሉን ማስቀጠል ተገቢ ነው ብለን በፅናት የምናምን ሰዎች ብንኖርም ዋናው የችግሩ ምንጭ መንግስት በሆነበት ሁኔታ ሁሉም ህዝብ እንደ እኛ ለምን ለሰላማዊ ትግል ታማኝ ሆኖ አይቀጥልም ብለን ልንከራከር አንችልም።

ይህንን የመከራከር አቅም ያሳጣን የመንግሥት የጦረኝነት አመለካከትና ድርጊት ነው። ከዚህ እውነታ ጋር በተያያዘ በወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሂደት ሁለቱም የትግል ስልቶች በጣምራ እየተካሄዱ መሆናቸው ነባራዊ ሁኔታው የፈጠረው ክስተት መሆኑን ለመቀበል ተገደናል። ለዚህም ነው ተገደው ወደ ትጥቅ ትግል የገቡትን ኃይሎች ከመቃወምና ከማውገዝ ይልቅ በቅድሚያ የችግሩ ዋና ፈጣሪ በሆነውና ችግሩን የመፍታት ተቀዳሚ ግዴታ ባለበት፣ ለችግሮቹም ሰላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ የመስጠት ሰፊ ዕድል እጁ ላይ ባለው በመንግስት ላይ ጫና መፍጠርን የመረጥነው። መንግሥት ህግ የማክበርና የማስከበር ኃላፊነቱን በአንፃራዊነት ለመወጣት የሚጥር ቢሆን ኖሮ ግን ቀዳሚው ትችታችንና ተቃውሞአችን በታጣቂ ኃይሎች ላይ በሆነ ነበር።

በአጠቃላይ የወቅቱን አቋማችንን የያዝነው የመንግስትን ጥፋተኝነትና ጠብመንጃ ለማንሳት የተገደዱትን ኃይሎች መገፋት በመረዳትና በማወቅ ነው እንጂ እንዲህ ዓይነቱን ምክንያት ተከትሎም የሚካሄድ የትጥቅ ትግል ለአገራችን ይጠቅማል ወይም ዘላቂ መፍትሄ ለማምጣት ያስችላል የሚልና ከመርሃችን የሚቃረን እምነት ኖሮን አይደለም። በኛ እምነት ታጣቂ ኃይሎቹ አሳማኝ ምክንያት ያላቸው ህልውናቸውን ለማስጠበቅ ሲሉ ጫካ ገብተው ለመዋጋት ስለመገደዳቸው ነው እንጂ የትጥቅ ትግል ለአገራችን አዋጭና ተገቢ ነው ብለው ስለማመናቸው አይደለም።

ለዚህም ነው ታጣቂዎቹ ለህልውናቸው መጠበቅ አስተማማኝ መፍትሄ ወይም ዋስትና ከመንግስት እስኪያገኙ ድረስ መዋጋታቸው ምክንያታዊ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ሁልጊዜም ግን በራቸውን ለሰላማዊና ፖለቲካዊ መፍትሄ ወይም ሃቀኛ ድርድር ክፍት እንዲያደርጉ እየተማፀንን የምንገኘው። የእኛ ምርጫ ሰላማዊ ትግል ሆኖ እያለ አንዳንዶቻችን በአገሪቱ እየተካሄዱ ባሉት የትጥቅ ትግሎች ዙሪያ ሃሳብ ለመስጠት የምንገደደውና ስልቱን ስለምንደግፍ ሳይሆን ከኛ ፍላጐትም ውጭ የሚካሄድ የትጥቅ ትግል የሚያስከትለው ውጤት የእኛንም ሆነ የአገሪቱን ዕጣ-ፈንታ የሚወስን በመሆኑ ነው።

በሰላማዊ ትግል የምናምነው ኃይሎች የታጣቂ ኃይሎቹን ምክንያታዊነት በዚህ መጠን ለመረዳት የቻልን ቢሆንም በታጣቂ ኃይሎቹ በኩል ግን በዚያው መጠን የሰላማዊ ትግልን አስፈላጊነት ለመገንዘብ የቻሉ አይመስሉም። አብዛኛዎቹ ታጣቂ ኃይሎች የራሳቸው ምክንያታዊ ምርጫ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከመጣር አልፈው ሰላማዊ ትግልን በጭፍን ሲቃወሙና ሲያወግዙ እያየን ነው። አንዳንዶቹ ታጣቂዎችና ደጋፊዎቻቸው በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ ሊካሄድ ታስቦ የነበረውን "ጦርነት እንዲቆም የሚጠይቅ ሰላማዊ ሰልፍ" በአደባባይ ለመቃወም ሲደፍሩ ጭምር ታይቷል። ይህ የማይገባ፣ ለማናችንም የማይጠቅምና ምክንያታዊ ያልሆነ አቋም ነው። እንዲህ ዓይነቱ አቋም ከማንም በላይ የሚጠቅመው ገዥውን ፓርቲ ነው።

በራሳችንም ሆነ በሌላው ዓለም በተደጋጋሚና በበቂ ሁኔታ እንደታየው የኢትዮጵያ የፖለቲካ ሁኔታም ወደ ሰላማዊ ትግል መስመር የማይገባ ከሆነ ተያይዘን ከመተላለቅ ባለፈ ዘላቂ መፍትሄ ለአገራችን ልናመጣ አንችልም። ስለሆነም ታጣቂ ኃይሎች ሰላማዊ ትግልን በጭፍን ከመቃወምና ከማውገዝ ሊቆጠቡ ይገባል። መንግስት ሰላማዊ ትግልን የሚፈራበትና ለማፈን የሚሞክርበት ምክንያት ግልፅ ነው። ለስልጣን የበላይነቱና ቀጣይነቱ አደገኛ ነው ብሎ ስለሚያምንና በርግጥም ስለሚጐዳው ሰላማዊ ትግልን አብዝቶ መፍራቱና ለማፈን መሞከሩ የሚጠበቅ ነው።

ነገር ግን የአገራችን ታጣቂ ኃይሎች የራሳችሁን ምርጫ ይዛችሁ መቀጠል እየቻላችሁ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የሰላማዊ ትግሉ መቀጠል ለትግሉ መጠናከርና መፋጠን የማይተካ ሚና ያለው ከመሆኑም በላይ

ለራሳችሁም የመታገያ አጀንዳ በማቀበል ረገድ አዎንታዊ ፋይዳ ያለው መሆኑ እየታወቀ የሰላማዊ ትግል ተቃዋሚ ሆናችሁ መገኘታችሁ ትልቅ ስህተትና እንቆቅልሽ ነው። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ እየተካሄደ ባለው የትጥቅ ትግል የሚሳተፉት ዜጐቻችን ቁጥር ከአጠቃላዩ ህዝብ ቁጥር ከ1 በመቶ በታች የሆነ ነው። ስለዚህ “ሌላው ህዝብ የተጠናከረ ሰላማዊ ትግል ማካሄድ ቢችል የምንጐዳው እኛ ነን ወይስ አገዛዙ?” የሚለውን ጥያቄ ራሳችሁን ጠይቃችሁ ለራሳችሁ አሳማኝ መልስ መስጠት ይበጠቅባችኋል።

ማርቲን ሉተር ኪንግ ከብዙ ዓመታት በፊት እንዳለው ሰላማዊ ትግልና የኃይል አማራጭ ለምርጫና ለንፅፅር መቅረብ የሚገባቸው ስልቶች አይደሉም። ሰላማዊ ትግል ህልውናን የማስቀጠል ምርጫ ሲሆን፣ የኃይል-ተኮር ትግልና ጦርነት ግን ህልውናን የበለጠ አደጋ ላይ የመጣል ምርጫ ነው። የአገራችን ታጣቂ ኃይሎች ይህንን እውነታ በውል በመረዳት እይታችሁን ልታስተካክሉ ይገባል።

# መደምደሚያ

**“ችግሮቹ በተፈጠሩበት ተመሳሳይ አስተሳሰብ ችግሮቹን ለመፍታት መሞከር ስህተት ነው”** -*[አልበርት አንስታይን]*

በዚህ መጣጥፍ ለማየት እንደተሞከረው ሰላማዊ ትግል ከትጥቅ ትግል ጋር ሲነፃፀር ከሞራልም ሆነ ከስልት ውጤታማነት አኳያ በብዙ ርቀት ተገቢና አዋጭ ስልት ነው። ሰላማዊ ትግል ተገቢና አዋጭ እንዳልሆነ ለማሳመን በአሁኑ ወቅት እየቀረቡ ያሉት መከራከሪያዎች አሳማኝ እንዳልሆኑ፣ እንዲያውም ሰላማዊ ትግል በበቂ ዝግጅትና በተደራጀ ሁኔታ ከተመራና ከተካሄደ በአጭር ጊዜ፣ በአንፃራዊነትም በቀላል መስዋዕትነት ዘላቂ ውጤት ለማምጣት በሚያስችል አግባብ ስኬታማ ሊያደርገን እንደሚችል ከበቂ በላይ በሆኑ ምሳሌዎችና ተሞክሮዎች ለማየት ችለናል።

በአንፃሩ የእርስ-በርስ ጦርነት አሁን ለምንገኝበት ሁለንተናዊ ኋላ-ቀርነት ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ፣ ጦርነት ቢበዛ በስልጣን ላይ ያለን መንግስት ከስልጣን ከማውረድ ባለፈ ዘላቂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማምጣት እንደማያስችል፣ ከዚያም በላይ ጦርነት በትውልዶች ላይ አስከትሎት የሚያልፈው የስነ-ልቦና ስብራትና ቁስል ከባድና በቀላሉ መፈወስ የማይችል እንደሆነ ለማየት ሞክረናል። ጦርነት በዚህ መጠን የማይገባና አዋጭ ያልሆነ ስልት መሆኑን ከራሳችንም ሆነ ከሌላው አለም የታሪክ ሂደት ከተረዳንም በኋላ እኛ ላይ ሲደረስ የተለየና አዲስ ውጤት ያመጣ ይመስል ዛሬም በባሰ ሁኔታ አጠናክረን ቀጥለንበታል።

በአሁኑ ወቅት የገባንበት ጦርነት በመጠኑም ሆነ በይዘቱ ካለፉት ሁሉ የባሰና የተወሳሰበ ሆኗል። የወቅቱ ጦርነት በፖለቲካ ፅንፈኝነት ወይም በርዕዮተ-ዓለም ቅራኔ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በዋናነት በብሄርተኝነት ስሜት የሚካሄድ ስለሆነ በመንግስትና በህዝብ መካከል ብቻ ሳይሆን የጐንዮሽ የህዝብ-ለህዝብ ትግል የሚካሄድበት ሆኗል። በብሄርተኝነት ስሜት የሚካሄድ ጦርነት በየትኛውም ዓይነት ሌላ ምክንያት ከሚካሄድ ጦርነት ይልቅ የከፋ ውጤት የሚያስከትል በመሆኑም እርስ-በርስ መገዳደላችን አልበቃ ብሎ ዓለምን ባስደነገጠ ሁኔታ በጭካኔ የአገዳደል ዓይነትና መጠን የምንፎካከርም አድርጐናል።

በአሁኑ ወቅት በአገራችን እየተካሄደ የሚገኘው ጦርነት በፍጥነት ጅምላ ጨራሽ ከመሆኑም በላይ በይዘቱ በከፍተኛው የግጭት ወይም የጦርነት ደረጃ ሊመደብ የሚችል ነው። የወቅቱ ጦርነት “ይለይልን!” ከሚል ፉከራ ጀምሮ “በውጤቱ በሚሊዮኖች ቢያልቁም ሆነ አገሪቱ ብትፈርስ ግድ የለኝም” በሚል የጦዘ የብሄርተኝነት ስሜት ጭምር የሚካሄድ በመሆኑ በቀላሉ በድርድርና በእርቅ

መፈታት ወደማይችልበት አደገኛ ደረጃ እየተሸጋገረ ይገኛል። ምክኒያቱም የወቅቱ ጦርነት በአባቶቻችን ዘመን ሲሆን እንደነበረው ለአንድ ውስን ዓላማ፣ በአንድ አዋጅ፣ በአጭር ጊዜ የፉከራና የቀረርቶ ቅስቀሳ የተገባበት ጦርነት አይደለም።

ይህ የእርስ-በርስ ጦርነት በታሪካችን አይተነው በማናውቀው መጠን ለአስርት ዓመታት በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በማህበራዊ ሚዲያ፣ በምስልና በድምፅ ተቀናብረው በተሰሩ ዘፈኖችና ድራማዎች ትውልዱ በብሄርተኛነትና በጦረኛነት ስሜት በመንግስትና በተቃዋሚው ጐራ መካከል እንዲቀሰቀስ ብቻ ሳይሆን እንዲታነፅ ከተደረገ በኋላ የተከሰተ ጦርነት ነው። ይህ ጦርነት በጊዜያዊ ምክንያቶች በድንገት የፈነዳ ሳይሆን ተፈልጐና የረዥም ጊዜ አድካሚ ስራ ተሰርቶ የመጣ ውጤት ነው። ለዚህም ነው ፖለቲከኞችና ታጣቂ ኃይሎች ብቻ ሳይሆኑ ቄሱ፣ ሼኩ፣ አትሌቱ፣ አርቲስቱ፣ ምሁራኑ፣ አዛውንቱ፣ ወጣቱና ከ10 ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ሳይቀሩ የጦርነት አወዳሽና ቀስቃሽ ሆነው ያየናቸው።

በዚህ ሁኔታ የገባንበት የወቅቱ ጦርነት የመጨረሻ ውጤቱ እንዳለፉት ጦርነቶች ነባር ችግሮቻችንን በማስቀጠል ወይም ከአንድ አምባገነን አገዛዝ ወደ ሌላ አገዛዝ በማሸጋገር ብቻ የሚጠናቀቅ ሳይሆን እንደ አገርና ህዝብ አጠቃላዩን ህልውናችንን የማጥፋት ሰፊ ዕድል እንዳለው ግልፅ እየሆነ መጥቷል።

ኢትዮጵያውያን እዚህ ላይ ቆመንና ከስሜታዊነት ወጣ ብለን ከዚህ በታች የቀረቡትን አምስት አንኳር ጥያቄዎች እንደ ትውልድ ራሳችንን መጠየቅ አለብን።

1ኛ. ጦርነት ለችግራችን ዘላቂ መፍትሄ እንደማያመጣ ለማወቅ ሌላ ስንት ዓመት መዋጋት ያስፈልገናል?

2ኛ. በጦርነት አንዳችን ሌላችንን በዘላቂነት ማሸነፍ እንደማንችል አምነን ለመቀበልና ለሃቀኛ ድርድር ለመቀመጥ ሌላ ስንት ሚሊዮን ዜጐቻችን ማለቅ አለባቸው? ስንትስ የአገር ሃብትና ንብረት መውደም አለበት?

3ኛ. እንደ የ21ኛው ክፍለ ዘመን ትውልድ አባልነታችንስ አገሪቱን ከጦርነት አዙሪት ማውጣት ካልቻልን ካለፈው ትውልድ የተሻለ ለልጆቻችን የምናወርሰው ምን አዲስ ታሪክና እሴት ይኖረናል?

4ኛ. የአገር ህልውናንና የህዝብን ደህንነት ከኛ የጥላቻ ስሜትና የስልጣን ጥያቄ አብልጠን ማየት እንዴትና ለምን ተሳነን?

5ኛ. አብዛኛው የዓለም ህዝብ ችግሮቹን በሰላማዊ መንገድ እየፈታ በሚገኝበት በአሁኑ ዘመን እኛን ከጦርነት አዙሪት እንዳንወጣ ያደረገን መሰረታዊ ምክንያት ምንድን ነው? የስነ-ልቦና መታወክ፣ ወይንስ የማሰብ ችሎታ መቀንጨር?

ኢትዮጵያውያን እነዚህን ጥያቄዎች በአግባቡና በድፍረት መልሰን አገራችንን ከጦርነት አዙሪት በአስቸኳይ ካላወጣን በስተቀር ህዝባችንን ከእልቂት፣ አገራችንንም ከመፍረስ ልናድን አንችልም። የገባንበት ችግር እጅግ ከባድና የተወሳሰበ በመሆኑ ምክንያት በቀላሉ በሰላም ለመፍታት የሚያስቸግር ቢሆንም የአገራችንም ሆነ የራሳችን ህልውና መቀጠል ካለበት ግን ችግራችንን በሰላም መፍታት የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን ግዴታ ነው።

ይህ የሞራል ምርጫ ብቻ ሳይሆን በተግባር ውጤታማ ለመሆን የመቻልም /Pragmatic/ ምርጫ ነው። የኢትዮጵያ የፖለቲካ ልሂቃን ሰላማዊ ትግል የሚጠይቀውን ዋጋ ለመክፈል ከልባችን ከወሰንን ይህንን አገዛዝ በአጭር ጊዜ፣ በአንፃራዊነት በቀላል መስዋዕትነትና ለዘላቂ ውጤት በሚያበቃ አግባብ

ማሸነፍ የማንችልበት ምክንያት የለም። ለአንድ ትግል አሸናፊነት ዋና ቅድመ ሁኔታ የሆነው የህዝብ ድጋፍ እንዳለን የማንጠራጠር እስከሆነ ድረስ (እኔ አልጠራጠርም) ይህንን በማያከራክር መጠን በህዝብ የተጠላና የተናቀ ደካማ አገዛዝ በሰላማዊ ትግል ከማሸነፍ የሚያግደን ምንም ዓይነት ምድራዊ ኃይል አይኖርም።

ወቅቱ ለችግራችን ሁሉ ዋና መነሻ ምክንያት የሆነውን የጥላቻና የጦርነት አዙሪት በማስቀጠል እልቂታችንንና መፍረሳችንን የበለጠ ፈጣንና አይቀሬ የምናደረግበት ሊሆን አይገባም። ጦርነትን በማስቀጠል ከእስካሁን በተለየ የምናመጣው አዲስና የተለየ መፍትሄ አይኖርም። አልበርት አንስታይን እንዳለው “ተመሳሳይ ድርጊት ደጋግሞ በመፈፀም የተለየ ውጤት መጠበቅ ቀውስነት ነው”። ምክንያቱም ከእስካሁን በተለየ መንገድ /Out of the Box/ አዲስ ነገር ማሰብና መሥራት ካልቻልን በስተቀር ችግሩ ቀድሞ በተፈጠረበት ተመሳሳይ መንገድ ዛሬ ላይ ሊፈታ አይችልም። ልናመጣው ስለምናስበው የመጨረሻ ውጤት ብቻ ሳይሆን ወደ ውጤቱ ስለምንሄድበት ሂደትም ተጨንቀን ማሰብ አለብን።

“መድረሻ ውጤቱ የስልቱን ትክክለኛነት ያረጋግጣል” የሚለው የኒኮላ ማኪያቬሊ አባባል ጊዜ ያለፈበት የ16ኛው ክፍለ ዘመን አስተሳሰብ ነው። ወደፊት ነፃ እናወጣሃለን፣ ወይም እናበለጽግሃለን የምንለውን ህዝብ መቋጫ በሌለው የጦርነት አዙሪት እያስጨረስን መቀጠል ከሞራልም ሆነ ከውጤታማነት አኳያ እጅግ በጣም የተሳሳተ ስልት ነው። በጦርነትና ጦርነት ባስከተለው ጣጣ አገሩን ለቆ እየተሰደደና በረሃብ እያለቀ ያለን ህዝብ መቼ? እንዴትና ከማን ነው ነፃ የምናወጣው? መቼስና እንዴት ነው የምናበለጽገው? ከምድረ-ገፅ ከጠፋ በኋላ?

በአጠቃላይ፣ በዘላቂነት አሸናፊ በማይኖረው ጦርነት ውስጥ ቀጥለን ዘላቂ መፍትሄ ማምጣት እንደማንችል ከልባችን ተስፋ በመቁረጥ ጦርነትን በሃቀኛ ድርድር በአስቸኳይ ማቆምና ከስነ-ልቦናዊ ስብራትና ቁስል አድኖ ለዘላቂ መፍትሄ ወደሚያበቃን ሃቀኛና ሁሉን አቀፍ አዲስ የሽግግር ሂደት ውስጥ መግባት አለብን። ይህንን ማድረግ አለመቻል የሽንፈቶች ሁሉ ሽንፈት፣ የውድቀቶች ሁሉ ውድቀት ሲሆን “ሚሊዮኖችን ያስጨረሰ፣ ሚሊዮኖችን ያሰደደና የአገሪቱን ህልውና ያፈረሰ ደካማና ክፉ ትውልድ” በመባል በመጭው ትውልድና በታሪክ ፊት ተወቃሽና ተጠያቂ ያደርገናል።

ዛሬ ላይ ሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ የችግሩ አካል ስለሆንን ከዚህ ተጠያቂነት ለመዳን የሚያስችል ሃሳብና ድርጊት የምናዋጣ ዜጎች እንሁን።

**ጦረኝነትና ጦርነት ከምድራችን ይወገዱ…!**

**ልደቱ አያሌው**

መጋቢት 11 2016 ዓ.ም